# አማርኛ

## እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ

## የተማሪ መጽሐፍ

## 4ኛ ክፍል


**አዘጋጆች**

ግሩም ጥበቡ

ከበደ አየለ

**አርታኢዎች**

እሸቱ ኢጋ

አንበሴ በቀለ

**ጥራት ተቆጣጣሪዎች**

ይልፋሸዋ ጥላሁን

በርናባስ ደበሎ

ታምሩ ገለታ

**ግራፊክስ እና ምሥል ገለፃ**

ሰለሞን አለማየሁ ጉተማ

© የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ 2014ዓ.ም.

ይህ መፅሐፍ በ2014 ዓ.ም በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ እና በነቀምቴ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በትብብር የተዘጋጀ ነው። የመጽሐፉ ህጋዊ የቅጂ ባለቤት ©2014 ዓ.ም. የኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ ነው። መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የዚህን መጽሐፍ ክፍል በተለያዩ መሳሪያዎች ያለባለቤቱ የቅድሚያ ፈቃድ እንደገና ማሳተም፣ ማሰራጨት፣ ማከማቸትና መልሶ መጠቀም አይቻልም።

የስዕሎችን የቅጂ መብቶች ለማክበር በተቻለን መጠን የሚፈለግብንን ጥረት ሁሉ አድርገናል። ሳናውቅ በስህተት ሳንጠቅሳቸው የተዘለሉ ካሉ በቅድሚያ ይቅርታ እየጠየቅን በሚቀጥሉት ህትመቶች አስፈላጊውን እውቅና እንደምንሰጥ ለመግለጽ እንወዳለን።

## ማውጫ

ማውጫ ........ iii
መቅድም ........ iv
መግቢያ ........ v
ምዕራፍ አንድ፡ የአካባቢ ጥበቃ ........ 1
ምዕራፍ ሁለት፡ የመንገድ ላይ ጥንቃቄ ........ 14
ምዕራፍ ሶስት፡ መረዳዳት ........ 26
ምዕራፍ አራት፡ ሥርዓተጸታ ........ 42
ምዕራፍ አምስት፡ ጉብኝት ........ 58
ምዕራፍ ስድስት፡ ስፖርት ........ 74
ምዕራፍ ሰባት፡ ውሃ ........ 91
ምዕራፍ ስምንት፡ ድርድር ........ 104
ምዕራፍ ዘጠኝ፡ የመገናኛ ብዙሃን ........ 118
ምዕራፍ አስር፡ ንግድ ........ 131

## መቅድም

ትምህርት ሚኒስቴር “ጥራቱ የተጠበቀና እኩል ተደራሽነት ያለውን ትምህርት ለሁሉም ማዳረስ” በሚል ትኩረት ሰጥቶ አዲስ ስርዓተትምህርት ቀርጾ አቅርቧል። በዚህ መሠረት ቀድሞ በነበረው ሥርዓተትምህርት ላይ ታይቶ የነበረውን ክፍተት ለመሙላት ምርምር ተደርጓል። ከምርምሩ የተገኙ አቅጣጫዎችም የተማሪዎቹን ደረጃ አለመመጠን፣ የትምህርቱ አንኳር ጽንሰሀሳቦች ግልጽ አለመሆን፣ ከይዘቱ መታጨቅ የተነሳ ለዓመቱ ከተመደበለት ክፍለጊዜ ጋር አለመመጣጠን እና ከተጓዳኝ ሥርዓተትምህርቶች አማራጭ ግብዓቶችን አለመጠቀም ናቸው። ስለሆነም የአፍመፍቻ ቋንቋ ልህቀትን ለማሻሻል፣ በአውድ የተደገፈ ለማድረግ እና በተግባር ላይ የተመሰረተ የመማር ስኬትን ለማረጋገጥ ስርዓተትምህርቱ ተቀርጿል።

ስርዓተትምህርቱን መሠረት በማድረግ የትምህርት መማሪያዎች ተዘጋጅተዋል። ከእነዚህም ውስጥ የተማሪው መማሪያ መጽሐፍ አንዱ በመሆኑ ይህ አማርኛ እንደአፍመፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ሊዘጋጅ ችሏል። መጽሐፉም ተማሪዎች ቢያንስ መጎናጸፍ ያለባቸውን ብቃት (Minimum Learning Competency)፣ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶችን፣ ተግባቦታዊ የመማር ዘዴን መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ ነው።

ከዚህ አንፃር የዚህ መጽሐፍ ዝግጅት በቀድሞው የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ የተስተዋሉ ክፍተቶችን ይሞላል ተብሎ ይጠበቃል።

## መግቢያ

ይህ መማሪያ መጽሐፍ አስር ምዕራፎች አሉት። እያንዳንዱ ምዕራፍ ደግሞ በስሩ ስድስት ንዑስ የትምህርት ክፍሎችን አካቷል። እነዚህም ትምህርት ክፍል አንድ ማዳመጥ፣ ትምህርት ክፍል ሁለት መናገር፣ ትምህርት ክፍል ሶስት ማንበብ፣ ትምህርት ክፍል አራት መጻፍ፣ ትምህርት ክፍል አምስት ቃላት እና ትምህርት ክፍል ስድስት ሰዋስው ናቸው። እያንዳንዱ የትምህርት ክፍል በመርሃትምህርቱ በተደለደለው መሰረት በክፍለጊዜ ተከፋፍሎ የቀረበ ሲሆን በስሩ መመሪያዎች፣ ትዕዛዞች፣ መልመጃዎችና ተግባሮች አካቷል።

ከዚህ አኳያ የቋንቋ ክሂሎች የተደራጁት በቅድመተግባር፣ በጊዜ ተግባር እና በድህረተግባር ሂደታዊ አቀራረብ ነው። የቋንቋ የዕውቀት ዘርፎች ደግሞ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ እና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ ዘዴን ተከትለዋል።

በዚህ መሰረት የመማሪያ መጽሐፉ ማስተማሪያ ዘዴ ተማሪ ተኮር እንዲሆን ተደርጓል።

# ምዕራፍ አንድ፡ የአካባቢ

**ክፍለጊዜ፡ አንድ**

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

በዚህ ትምህርት ክፍል የማዳመጥ ጽሁፍ፣ የተለያዩ መልመጃዎች እና ተግባራት ስለቀረቡላችሁ በተሰጡት ትዕዛዛት መሰረት በትኩረት ስሩ።

### የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

ሀ. በአካባቢያችሁ ችግኝ ተክላችሁ ታውቃላችሁ?

ለ. ችግኝ መትከል፣ አካባቢን ማስዋብና ማጽዳት

በአጠቃላይ ምን ተብሎ የሚጠራ ይመስላችኋል?

### የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

እያዳመጣችሁ ሰንጠረዡን አሟሉ።

| ጥሩነሽ እና ጓደኞቿ | ያከናወኗቸው ተግባራት |
|---|---|
| መጀመሪያ | |
| በቀጣይ | |
| መጨረሻ | |

ክፍለጊዜ፡ ሁለት

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

**ሀ. በምንባቡ መሰረት በቃል መልሱ።**

1. ጥሩነሽ የአካባቢ ጥበቃ ክበብ ለማቋቋም ያቀደችው ከማን ጋር ነው?
2. ለነጥሩነሽ አስፈላጊ ድጋፍ ያደረጉት ማን ናቸው?
3. በጽሁፉ ውስጥ “የተራቆተው …” የሚለው ቃል ምንን ለመግለጽ የገባ ይመስላችኋል?
4. እነጥሩነሽ ሽልማት ያበረከተላቸው አካል ማን ነው?
5. ከጥሩነሽ ታሪክ ምን ተማራችሁ?

**ለ. ባዳመጣችሁት መሰረት “እውነት” ወይም “ሐሰት” በማለት መልሱ፤ መልሳችሁን በምክንያት አስደግፉ።**

1. የእነጥሩነሽ ዕቅድ የጀመረው ከትምህርት ቤታቸው ውጪ ነው።
2. ርዕሰ መምህርቷ በነጥሩነሽ ሀሳብ አልተስማሙም።
3. በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ አገር በቀል ችግኞች

ተተከሉ።

4. እነጥሩነሽ የትምህርት ቤቱን ግቢ በችግኞች ለመሸፈን ወር አልፈጀባቸውም።
5. "የአካባቢ ጥበቃ ጀግና" የተባለችው ጥሩነሽ ነች።

**ክፍለጊዜ፡ ሶስት**

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### ተግባር አንድ



በስዕሉ የምትመለከቷቸው ሰዎች ምን እየሰሩ እንደሆነ በቡድናችሁ ከተወያያችሁ በኋላ ተራ በተራ እየተነሳችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

**ክፍለጊዜ፡ አራት**

## ተግባር ሁለት

በአካባቢያችሁ የአካባቢ ጥበቃ ስራ ጎብኟታችሁ የስራውን ዓይነት (የችግኝ ተከላና እንክብካቤ፣ የአካባቢ ጽዳት፣ የአፈር ጥበቃ ስራ)

- ስራው ያለበት ደረጃና ስራው በማን እንደሚከናወን መረጃ ሰብስቡ፤
- በመቀጠል ዘገባውን አደራጁ፤
- በመጨረሻም የቃል ዘገባ ለጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

**ክፍለጊዜ፡ አምስት**

## ተግባር ሶስት

ከዚህ በታች ደን ጭፍጨፋንና የሚያስከትለውን ጉዳት በተመለከተ የመነሻ ሀሳቦች ቀርበላችኋል። በመሆኑም በቡድናችሁ ተወያይታችሁ በተወካያችሁ አማካኝነት አጭር ንግግር አድርጉ።

- ደን ጭፍጨፋ ምን እንደሆነ
- ምን ምን ጉዳቶች እንደሚያስከትል
- በጉዳቱ እነማን ተጠቂ እንደሚሆኑ
- ለመከላከል የሚወሰድ እርምጃ

**ክፍለጊዜ፡ ስድስት**

# ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ



1 ድሮ



2 አሁን

## የቅድመማንበብ ጥያቄዎች

1. በአካባቢያችሁ ደን አለ?
2. ካለ ደኑ በምን ሁኔታ ላይ ይገኛል?
3. ስለምስሉ ያስተዋላችሁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

## ደን

የአገራችን የደን ይዞታ ባለፉት 50 እና 60 አመታት ከነበረበት አንፃር ሲታይ በጣም ቀንሷል። **ቀላል የማይባሉ** አከባቢዎች **ጥቅጥቅ ያለ** ደናቸውን **እንደዋዛ** አጥተዋል።

ለደን መመናመን በርካታ ምክንያቶች ሊጠቀሱ ይችላሉ። ከምክንያቶቹ መካከልም ደን ለማገዶ መቁረጥ አንደኛው ነው። ሌላኛው ደግሞ ሰዎች የእርሻ ቦታ ፍለጋ ሲሉ **ምንጣሮ**

ማካሄዳቸው ነው። እንዲሁም የግጦሽ ቦታ ፍለጋና የመሳሰሉት ለደን ውድመት ተጠቃሾች ናቸው።

የደን መጨፍጨፍ የተለያዩ ችግሮችን ያስከትላል። ከነዚህም መካከል በዝናብ ወቅት ለም አፈርን **በመሸርሸር** ወደ ሌላ ቦታ እንዲወሰድ ያደርጋል። በተጨማሪም በውስጡ ይኖሩ የነበሩ የዱር እንስሳትን **እንዲሰደዱ** ያደርጋል። ለበረሃማነት ወይም ለድርቅና ለጎርፍ አደጋም ያጋልጣል። በአጠቃላይ የደን መጨፍጨፍ የምድር ስነምህዳር **እንዲናጋ** ያደርጋል።

| |
|---|
| 1. የደን መመናመን ምክንያቶችን ዘርዝሩ። |

የደን መውደም የሚያስከትላቸውን ችግሮች ከተረዳንና አሳሳቢነቱ ምን ያህል እንደጨመረ ካወቅን፣ ቀጣዩ ነገር ምን እናድርግ የሚለው ነው። እየወደሙ ያሉ ደኖችን **ለመታደግና** የአካባቢ ሚዛንን ለማስጠበቅ ተከታዮቹን እርምጃዎች መውሰድ ይገባል። እነሱም፡- ዛፎችን **ያለአሳማኝ** ምክንያት አለመቁረጥ፣ በቆረጥናቸው ዛፎች ምትክ ሌሎችን አብዝቶ መትከል ናቸው።

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

**ሀ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥቅል ሀሳቦች በምንባቡ መሰረት ዝርዝር ሀሳብ ስጧቸው።**

1. ለደን መመናመን ምክንያቶች …

   ምሳሌ፡ ለማገዶ መቁረጥ…

2. የደን መጨፍጨፍ የተለያዩ ችግሮች…

   ምሳሌ፡ ለም አፈር መሸርሸር…

3. እየወደሙ ያሉ ደኖችን ለመታደግና የአካባቢ ሚዛንን ለማስጠበቅ የሚወሰዱ እርምጃዎች…

   ምሳሌ፡ ችግኝ መትከል…

**ክፍለጊዜ፡ ስምንት**

**ለ. በምንባቡ መሰረት በቃል መልሱ።**

1. ለደን መመናመን መንስኤ ምንድን ነው?
2. ለም አፈርን በመሸርሸር ወደ ሌላ ቦታ የሚወስደው ምንድን ነው?
3. በምንባቡ "የምድር ስነምህዳር እንዲናጋ ያደርጋል" ሲል ምን ማለቱ ነው?

4. በአንቀጽ ሶስት “ለመታደግ…” የሚለው ቃል አውዳዊ ፍች ምንድን ነው?
5. በአንቀጽ ሁለት “ይህም” የሚለው ቃል ምን ያመለክታል?

**ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ**

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

### መልመጃ ሶስት

**ሀ. በሰንጠረዡ ውስጥ ተጣምረው የመጡ ቃላትን በአንድ ዓረፍተነገር አዋቅራችሁ ጻፉ።**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ቀዳ/ሞላ | በላ/ጠገበ | ነቀለ/ተከለ | ተነሳ/ሄደ |
| ታጠበ/ጠረገ | | | |

ምሳሌ፡ ገመቹ ከእንቅልፉ ተነሳ እና ወደትምህርት ቤት ሄደ።

**ክፍለጊዜ፡ አስር**

**ለ. ከዚህ በታች የቀረቡ ዓረፍተነገሮችን አስተካክላችሁ መልሳችሁ ጻፉ።**

1. ችግኝ ተከለች እና ሔዋን ተንከባከበች።
2. ስራ ናኦል አግዘን አጥና ወይም።
3. ጥናት ያጠናል ነገር ግን ገመቹ ፈተና አላለፈም።
4. ታመመች አልማዝ በመሆኑም ሄደች ወደሀኪም ቤት።
5. አለብን ማጽዳት ቆሻሿል ሰፈራችን ስለዚህ።

ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ

# ትምህርት አምስት፡ ቃላት

## መልመጃ አራት

**ሀ. በ "ሀ" ስር ለቀረቡት ቃላት ፍችያቸውን ከ "ለ" ስር በመምረጥ አዛምዱ።**

| "ሀ" | "ለ" |
| --- | --- |
| 1. መጋራት | ሀ. መዋብ፣ ማማር |
| 2. ስነምህዳር | ለ. በሽታ (መአዛ) መሙላት |
| 3. ማሽብረቅ | ሐ. ከሌላ ቦታ ያልመጣ |
| 4. ማወድ | መ. ባዶ መሆን፣ መጥፋት |
| 5. መራቆት | ሠ. በብዛት መሄድ |
| 6. አገር በቀል | ረ. በተወሰነ ስፍራ የሚጠቃለሉ ህይወት ያላቸውና የሌላቸው ነገሮች |
| 7. መቦረቅ | ሰ. መካፈል፣ መስማማት |
| 8. መጉረፍ | ሸ. በደስታ መዝለል፣ መፍነክነክ |

ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት

**ለ. ቀጥለው ከቀረቡት ቃላትና ሀረጋት በመምረጥ ባዶ ቦታውን አሟሉ።**

| | | |
| --- | --- | --- |
| ለመታደግ | ደኖችን | በመሸርሸር |
| ጥቅጥቅ ያለ | ውድመት | |

1. የተበከለ አየር ልቀትን ከወዲሁ ካልተቆጣጠርነው በምድራችን ላይ ከፍተኛ __________ያስከትላል።
2. የዱር እንስሳትን ህይወት ________መረባረብ ያስፈልጋል።
3. ጎርፍ መሬታችንን ___________ምርታማነታችንን ይቀንሰዋል።
4. እዚያ ማዶ ያለ ስፍራ ለመድረስ __________ ጫካ ማቋረጥን ይጠይቃል።
5. አሳማኝ ምክንያት ከሌለን በስተቀር __________ መመንጠር የለብንም።

**ሐ. በአረፍተነገሮቹ ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት ወይም ሀረጋት አውዳዊ ፍች ስጡ።**

**ምሳሌ፡**

ልጁ በደንብ ባለማጥናቱ ፈተናውን **ወደቀ**።

(አላለፈም፣ ውጤት አላመጣም)

1. ተክሎችን መትከል እና መንከባከብ **ይጠበቅብናል**።
2. የደኖች መመናመን የአየር **መዛባትን** ያስከትላል።
3. ዛፎችን በመትከል ሁሉም **የድርሻውን** ሊወጣ ይገባል።

4. የአካባቢ <u>መራቆት</u> ለድርቅ ያጋልጣል።
5. በህይወታችን ብዙ <u>ውጣ ውረድ</u> ያጋጥመናል።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሶስት**

**መ. ተመሳሳይ ቃልን በተለያዩ አውዶች በመጠቀም ዓረፍተነገር መስርቱ**

**ምሳሌ፡** 1. ሌባባ ወደ ዱባይ ለመሄድ **ቆረጠች**።

(ቆረጠች-ወሰነች)

2. ሲፈን በስህተት ዛፍ **ቆረጠች**።

(ቆረጠች- አስወገደች)

| | |
|---|---|
| 1. በላ | 5. ወንበር |
| 2. መሰረተ | 6. ተቃጠለ |
| 3. ሰበረች | 7. ወጣ |
| 4. መስመር | 8. ተመነዘረ |

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት**

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

**ማስታወሻ**

**ነጠላ ዓረፍተነገር አንድ ድርጊት ብቻ በውስጡ ያያዘ ነው።**

ምሳሌ፡ ሔኖክ ኳስ ተጫወተ።

**ድርብ ዓረፍተነገር ደግሞ ሁለት ድርጊቶችን በአያያዥ ቃላት አጣምሮ የያዘ ዓረፍተነገር ነው።**

ምሳሌ፡ ሔኖክ ሰውነቱን አሟሟቀና ኳስ ተጫወተ።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት**

## መልመጃ አምስት

**ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡትን ዓረፍተነገሮች ነጠላ እና ድርብ በማለት ለዩ።**

1. ፍራኦል ምሳውን በላና ወደትምህርት ቤት ሄደ።
2. አልማዝ ቅጠል ቀጠፈች።
3. ጌታቸው ከፈረስ ላይ ወደቀና ተሰበረ።
4. ግርማ ማሳውን አረሰ።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት**

**ማስታወሻ**

አያያዦች ሀረግን ከሀረግ ወይም ዓረፍተነገርን ከአረፍተነገር ለማያያዝ ያገለግሉናል።

ምሳሌ፡- እና፣ ወይም፣ ግን፣ ነገር ግን፣ ሆኖም…

**ለ. በቀረበላችሁ አያያዥ ቃላት ተጠቅማችሁ ተከታዮቹን አረፍተነገሮች እያሟላችሁ ፃፉ።**

| እና/ና፣ | ወይም፣ | ነገር ግን፣ | ስለዚህ፣ |
|---|---|---|---|

ምሳሌ፡ቁርሴን በላሁና ወደ ትምህርት ቤት ሄድኩ።

**አጥንቻለሁ ስለዚህ ጥሩ ውጤት አስመዘገብኩ።**

1. በእግሬ እመጣለሁ ________ጋሪ እሳፈራለሁ።
2. ቡድናችን ጥሩ ተጫውቷል________አላሸነፈም።
3. ዛሬ ራሴን አሞኛል_____ወደ ሀኪም ቤት እሄዳለሁ።
4. ከትምህርት ቤት መጣች ________ገላዋን ታጠበች።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት**

**ሐ. በተከታዮቹ አረፍተነገሮች ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ አያያዥችን ለይታችሁ በማውጣት ጻፉ።**

1. ነግራው ነበር ነገርግን ሳይሰማት ቀረ።(ምሳሌ፡ ነገርግን)
2. ሁለት እግር አለኝ ሆኖም ሁለት ዛፍ አልወጣም።
3. ገበያ ሄድኩና ሁለት ኪሎ ሽንኩርት ገዛሁ።
4. ከክፍሉ አንደኛ ወጥታለች ስለሆነም በቅርቡ ልትሸለም ነው።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

**መ. ቀጥሎ የቀረቡ አያያዥችን በመጠቀም አረፍተነገር መስርቱ።**

ነገርግን ወይም እና ሆኖም ስለዚህ

**ምሳሌ፡** የባሌ ብሔራዊ ፓርክን ወይም ሶፍ ዑመር ዋሻን ይጎበኛል።

# ምዕራፍ ሁለት፡ የመንገድ ላይ ጥንቃቄ

**ክፍለጊዜ፡ አንድ**

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

**በዚህ ትምህርት ክፍል መምህራችሁ ከመንገድ ላይ ጥንቃቄ ጋር በተያያዘ ጽሁፍ በማቅረብ እንድታዳምጡ ያዟችኋል፤ በመሆኑም መምህራችሁ በሚመሯችሁ መሰረት አዳምጣችሁ ቀጥሎ የቀረቡትን ተግባራትና መልመጃዎች ስሩ፡፡**

### የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

1. በአከባቢያችሁ የመኪና አደጋ ተከስቶ ከሆነ ሁኔታውን ለክፍል ተማሪዎች ተናገሩ።
2. በመንገድ ላይ ስትሄዱ መተግበር ያለባቸው የመንገድ ላይ ደንቦችን ተናገሩ።

### የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. መምህራችሁ የሚያሰሟችሁን መዝሙር በጥሞና አዳምጡ።
2. መምህራችሁ የሚያሰሟችሁን መዝሙር በመለማመድ ዘምሩ።

ክፍለጊዜ፡ ሁለት

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

**ሀ. ከመምህራችሁ ጋር በተለማመዳችሁት መዝሙር መሰረት "እውነት" ወይም "ሐሰት" በማለት መልሱ።**

1. የመዝሙሩ ርዕሰ "አሽከርክር ረጋ ብለህ" የሚል ነው።
2. መዝሙሩ የሚመክረው ከሹፌር ይልቅ እግረኞችን ነው።
3. መዝሙሩ ረጋ ብሎ ከመንዳትይልቅ ፍጥነትን ያበረታታል።
4. ለእግረኛ ቅድሚያ መስጠት አደጋን ይቀንሳል።
5. "በመኪና አደጋ ከማለቅ ይዳኑ" የተባሉት አካላት ሴቶች ህጻናት እና አረጋውያን ናቸው።

**ለ. ባዳመጣችሁት መዝሙር መሠረት ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ።**

1. የመዝሙሩ መልዕክት

   ሀ. ሾፌሮች የትራፊክ ፖሊሶችን እንዲያከብሩ

   ለ. ሾፌሮች ተጠንቀቀው እንዲነዱ

   ሐ. እግረኞች ሹፌሮችን እንዲፈሩ

   መ. ሕብረተሰቡ ሹፌሮችን እንዲያወግዙ

2. “መፍጠንና መቅደም አይደለም ችሎታ” ሲል ምን ማለት ነው?

ሀ. በፍጥነት መንዳት ለችግር ይዳርጋል

ለ. በፍጥነት በመንዳት መኪና መቅደም ችግር አይፈጥርም

ሐ. በፍጥነት ያልነዳ ሹፌር ሰነፍ ነው

መ. ፍሬን ካለ በፍጥነት መንዳት ጥሩ ነው

3. ሹፌሮች መጠቀም የሌለባቸው

ሀ. ምግብ መመገብ

ለ. ለስላሳ ወይም ውሃ መጠጣት

ሐ. ፍራፍሬ መመገብ

መ. አልኮል መጠጣት

4. በአንድ የመኪና ጉዞ ውስጥ ከባድ ኃላፊነት ያለበት ማን ነው?

ሀ. ተሳፋሪ ለ. ሹፌር

ሐ. የመንገደኛ ቤተሰብ መ. የሹፌር ቤተሰብ

5. ከሚከተሉት አንዱ በመኪና አደጋ የሚመጣ ጉዳት ነው።

ሀ. የንብረት ውድመት ሐ. የአካል መጉደል

ለ. የሰው ህይወት መጥፋት መ. ሁሉም

**ክፍለጊዜ፡ ሶስት**

**ሐ. የተሰመረባቸውን ቃላት አውዳዊ ፍች በቃል መልሱ።**

1. መኪና ስትነዳ <u>ትዕግስት</u> ይኑርህ፡፡

2. ተጠንቅቆ በማሽከርከር ከአደጋ <u>መዳን</u> ይቻላል፡፡
3. መኪና ስታሽከረክር <u>**አትቸኩል**</u>፡፡
4. የመኪና አደጋ <u>አካል</u> ያጎላል፡፡

**ክፍለጊዜ፡ አራት**

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### ተግባር አንድ

**ከዚህ በታች የቀረቡትን ሀሳቦች መነሻ በማድረግ በመጀመሪያ በቡድናችሁ ተወያዩባቸው። በመቀጠል የደረሳችሁበትን ማጠቃለያ ለክፍል ተማሪዎች በተወካያችሁ አማካኝነት በቃል አቅርቡ።**

- የመኪና አደጋ የሚያስከትለው ጉዳት
- ከሹፌሮች የሚጠበቁ ጥንቃቄዎች
- ከመንገደኞች የሚጠበቁ ጥንቃቄዎች

**ክፍለጊዜ፡ አምስት**

### ተግባር ሁለት

በጥንድ በመሆን ተራ በተራ የመዝሙሩን ግጥም ተናገሩ። በግጥሙ ውስጥ ያልገባችሁ ሃሳብ ካለ መምህራችሁን ጠይቃችሁ ተረዱ።

**ክፍለጊዜ፡ ስድስት**

### ተግባር ሶስት

የመኪና አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ የሹፌር እና የመንገደኛ ስህተቶችን በመለየት በያንዳንዳቸው ላይ በግል አጭር ንግግር አድርጉ።

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**

## ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

የሚከተለውን ምንባብ ጥንድ ጥንድ በመሆን አንድ አንድ አንቀጽ ተራ በተራ ድምጻችሁን በማሰማት አንብቡ። ጓደኛችሁ ሲያነብ ወይም ስታነብ በትክክል ያልተነበቡ ናቸው የምትሏቸውን ቃላት እና ሀረጋት በማስታወሻ ደብተራችሁ መዝግቡ።

### የመንገድ አጠቃቀም ስርዓት

በኢትዮጵያ የተለያዩ ቦታዎች በከፋ ሁኔታ የመንገድ ላይ አደጋዎች ይደርሳሉ። በዚህ አደጋም በየዓመቱ ብዙ ሰዎች ህይወታቸው ያልፋል። በጣም ብዙ ቁጥር ያላቸው ሰዎች የአካል ጉዳተኛ ይሆናሉ። ከነዚህ መካከል አብዛኛዎቹ እግረኞች ናቸው።

እግረኞቹ ለመኪና አደጋ የሚጋለጡት ከጥንቃቄ ጉድለት ነው። ይህንን አሳሳቢ ጉዳይ ለመቀነስ የመንገድ አጠቃቀም ስርዓትን

መከተል ያስፈልጋል። እግረኞች ሲሄዱም ሆነ ዜብራ ሲያቋርጡ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባቸዋል። ከሁሉም በፊት እግረኞች የመንገዱን ግራ ጠርዝ ይዘው መጓዝ ይኖርባቸዋል።ይህም ከፊት ለፊት የሚመጣውን መኪና ለማየት ይረዳል።

የመኪና መንገድ ለማቋረጥ ጥንቃቄ ማድረግ የሚገቡን ነገሮች ከዚህ ቀጥለው የሚቀርቡት ናቸው። መጀመሪያ ለእግረኛ ማቋረጫ ተብሎ ነጭ ቀለም የተቀባ ቦታ ወይም ዜብራ ካለ ማየት፣ በመቀጠል መኪኖቹ ለእግረኞቹ ቅድሚያ በመስጠት መቆማቸውን ማረጋገጥ፣ በመጨረሻም መኪና መንገዱን በፍጥነት እየተራመዱ ማቋረጥ ያስፈልጋል። እንዲሁም የትራፊክ መብራት ባለበት ቦታ መብራቱ መኪኖችን ሲያስቆም ማቋረጥ ተገቢ ነው። የትራፊክ መብራት በሌለበት ደግሞ በትራፊክ ፖሊስ በመታገዝ ማቋረጥ ይቻላል።

በአጠቃላይ በመንገድ ስንጓዝ የትራፊክ ደንቦችንና የመንገድ አጠቃቀም ስርዓቶችን መጠቀም አለብን።

**ክፍለጊዜ፡ ስምንት**

## ተግባር አራት

1. ምንባቡ ሲነበብ የመዘገባችኋቸውን ቃላት ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ።

2. ቃላቱን ወይም ሀረጋቱን አስተካክላችሁ መልሳችሁ ድምጻችሁን በማሰማት ለክፍል ተማሪዎች አንብቡ።

**ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ**

## ተግባር አምስት

የሚከተሉት ቃላት እና ሀረጋት ከመንገድ አጠቃቀም ስርዓት ጋር የተያያዙ ናቸው። በመሆኑም የቃላቱን ነባራዊ አጠቃቀም ከላይ ከአነበባችሁት የመንገድ አጠቃቀም ስርዓት ጋር በማዛመድ አብራሯቸው።

1. ዜብራ
2. የመንገድ ላይ የትራፊክ መብራት
3. የግራ ጠርዝ ይዞ መጓዝ
4. እግረኞች

**ክፍለጊዜ፡ አስር**

# ትምህርት አራት፡ መጻፍ

## መልመጃ አራት

**በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ያሉትን አያያዥ ቃላት ለይታችሁ በማውጣት ጻፉ።**

1. ውድ ህይወትን እና ክቡር አካልን ላለማጣት የመንገድ አጠቃቀም ስርዓትን ማክበር ያስፈልጋል።
2. መንገድን ለማቋረጥ በዜብራ ወይም በእግረኞች ድልድይ መጠቀም ያስፈልጋል።

3. እግረኞች የመንገዱን ግራ ጠርዝ ይዘው መጓዝ ይኖርባቸዋል፤ የቀኝ አቅጣጫን ይዘው የሚጓዙ ከሆነ ግን ለአደጋ ይጋለጣሉ።
4. ኅበዝ ተማሪዎች የመንገድ አጠቃቀም ስርዓትን ይተገብራሉ፤ ስለዚህ ሁልጊዜ ከአደጋ የተጠበቁ ናቸው።

**ለ. ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥንድ ዓረፍተነገሮችን አያያዥ ቃላት ተጠቅማችሁ ድርብ ዓረፍተነገሮች መስርቱ።**

1. የመኪና አደጋ ህይወትን ያሳጣል።

   የመኪና አደጋ ንብረትን ያወድማል።
2. ዋቆ እራቱን በላ።

   ዋቆ ተኛ።
3. ቶልቱ በትርፍ ጊዜዋ ታጠናለች።

   ቶልቱ ትጫወታለች።
4. በለጠ የመንጃ ፈቃድ ለማግኘት ተፈተነ።

   በለጠ የመሰናክል ፈተናን ማለፍ አልቻለም።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ**

# ትምህርት አምስት፡ ቃላት

## መልመጃ አምስት

**ሀ. ከዚህ በታች በቀረቡ ዓረፍተነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላት እና ሀረጋት አገባባዊ ፍች ስጡ።**

ምሳሌ፡ የመንገድን ግራ እና ቀኝ <u>በመቃኘት</u> ማቋረጥ ያስፈልጋል።

የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍች መመልከት ይሆናል። ምክንያቱም ግራቀኝ የሚለው ቃል መቃኘት የሚለውን ቃል ፍች መመልከት የሚለውን ይጠቁማል።

1. እግረኞች የመንገዱን ግራ <u>ጠርዝ</u> ይዘው መጓዝ አለባቸው።
2. ተሽከርካሪዎች <u>በሚመላለሱባቸው</u> መንገዶች የሚጓዙ እግረኞች መጠንቀቅ አለባቸው።
3. <u>እግረኞች</u> ለእግረኞች ተብሎ በተዘጋጀ መንገድ ካለ በዚያ መጠቀም ይኖርባቸዋል።
4. የመኪና መንገድ <u>ለማቋረጥ</u> የሚወሰዱ ጥንቃቄዎች አሉ።
5. መኪኖች ለእግረኞች ቅድሚያ ሰጥተው <u>ማሳለፍ</u> አለባቸው።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት**

**ለ. የሚከተሉትን ቃላት በመንገድ ትራፊክ መብራት የሚታዩ ቀለማት ናቸው። በመሆኑም ቃላቱን ከነባራዊ አጠቃቀም ጋር በማዛመድ አብራሯቸው።**

1. ቀይ　　2. ቢጫ　　3. አረንጓዴ

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሶስት

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋሰው

**ማስታወሻ**

ዓረፍተነገር ቃላት ወይም ሀረጋት በስርዓት ተቀናጅተው የሚመሰርቱት የቋንቋ መዋቅር ነው። ይህ መዋቅር ቢያንስ ባለቤት እና ማሰሪያ አንቀጽ ኖሮት የተሟላ መልእክት ሊያስተላልፍ ይገባል። ዓረፍተነገር ነጠላ እና ድርብ ሊሆን ይችላል።

ምሳሌ ቦረና ወደ ትምህርት ቤት ሄደ።
ቦረና ትምህርት ተማረ።

ሁለቱም ዓረፍተነገሮች ነጠላ ዓረፍተነገር ናቸው።ምክንያቱም በውስጣቸው አንዳንድ ድርጊት ስላላቸው ነው። እነሱም "ተማረ" እና "ሄደ" ናቸው።

ሁለቱ ዓረፍተነገሮች በአንድ ላይ ተጣምረው አንድ ዓረፍተነገር ሲመሰርቱ ደግሞ ድርብ ዓረፍነገር ይሆናል። ምሳሌ፡ ቦረና ትምህርት ቤት ሄዶ ትምህርት ተማረ፡፡

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት

## መልመጃ ስድስት

**ሀ. የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች ነጠላ ወይም ድርብ መሆናቸውን በመለየት ጻፉ።**

ምሳሌ፡ ቦንቱ ምሳዋን በላች። (ነጠላ)

ሌሊሴ ምሳዋን በልታ ወደ ትምህርት ቤት ሄደች።(ድርብ)

1. መገርሳ ውሃ ቀድቶ ገላውን ታጠበ።
2. መገርቱ ኳስ ተጫወተች።
3. በቀለ ወደ ቤቱ ሮጠ።
4. ኢፋ ብርጭቆውን አጠበ።
5. ከበቡሽ ሙዝ ልጣ በላች።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት**

## ተግባር ስድስት

የተለያዩ መጽሃፎችን በማንበብ ነጠላ እና ድርብ ዓረፍተነገሮችን በመለየት በደብተራችሁ ጽፋችሁ ለክፍል ተማሪዎች ድምጻችሁን በማሰማት አንብቡ።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት**

## መልመጃ ሰባት

**ሀ. የሚከተሉትን አያያዥ ቃላት በመጠቀም ከታች ያሉትን ዓረፍተነገሮች አሟሉ።**

| ስለዚህ፣ | ምክንያቱ፣ | ነገርግን፣ | እና፣ | አለበለዚያ |
|---|---|---|---|---|

1. ፈኔት የክፍል ስራዋን በፍጥነት ሰራች-------አሳረመች።
2. የአበበ አዝመራ ጠፍቷል፤ --------------- መሬቱ በደንብ አልታረሰም።

3. ቡርቃ ብዙ ምርት አምርቷል፤ ---------------- የምግብ ችግር አይኖርበትም።
4. ጥላሁን ብዙ የእርሻ መሬት አለው፤ --------------- አልተጠቀመበትም።
5. ፍራኦል የተመደበበትን ስራ በአግባቡ መወጣት አለበት፤ ----------- በህግ ይጠየቃል።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት**

**ለ.የሚከተሉትን ቃላት በመጠቀም ያልተሟሉትን ዓረፍተነገሮች አሟልታችሁ ጻፉ።**

ሄደች፣ አጨደ፣ ቆረጠች፣ ጠጣ፣ ሮጠ፣ በላ፣ ተከለች

1. አልማዝ ምሳዋን በልታ ወደ ትምህርት ቤት ------።
2. ጥላሁን ፈረሱን ለመቅደም በፍጥነት --------------።
3. ገላኔ የአትክልቱን ቦታ ቆፍራ ሽንኩርት ----------።
4. በዳሶ እህሉ ስለደረቀ በማጭድ ----------------።
5. ተክሉ ውሃ ስለጠማው ለስላሳ ------------------።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

## ተግባር ሰባት

አምስት ድርብ አረፍተ ነገሮችን መስርታችሁ ለመምህራችሁ ካሳያችሁ በኋላ ድምጽ በማሰማት ለክፍል ተማሪዎች አንብቡ።

# ምዕራፍ ሶስት፡ መረዳዳት

ክፍለጊዜ፡ አንድ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

በዚህ ትምህርት ክፍል ስር የማዳመጥ ችሎታችሁን እንድታሻሽሉ የሚያግዙ መልመጃዎችና ተግባራት ቀርበዋል። በመሆኑም በትእዛዛቸው መሰረት ስሩ። እያዳመጣችሁ አጫጭር ማስታወሻ ያዙ።

### የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

የቀጣዮቹን ቃላት ፍች ገምቱ።

| | | |
|---|---|---|
| መዛባት፣ | ዘለቄታዊ፣ | ማመቻቸት |

ሀ. ቀጣዮቹን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

1. የአካል ጉዳት ያለበት ሰው በቤታችሁ ወይም በአከባቢያችሁ አለ?
2. ማህበረሰቡ አካል ጉዳኞችን እንዴት ያስተናግዳቸዋል?
3. ለአካል ጉዳተኞች ድጋፍ አድርጋችሁ ታውቃላችሁ?
4. ስለአካል ጉዳተኞች ዋና ዋና ሀሳቦችን በማስታወሻ ደብተራችሁ መዝግቡ።

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

**ለ. ምንባቡን እያዳመጣችሁ መልሱ።**

1. አካል ጉዳት ጊዜያዊ ወይም __________ ሊሆን ይችላል።
2. የአካል ጉዳት በ _______ ወይም በ ________ ሊከሰት ይችላል።

**ክፍለጊዜ፡ ሁለት**

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

**ሀ. ባዳመጣችሁት ጽሁፍ መሰረት "እውነት" ወይም "ሐሰት" በማለት በቃል መልሱ።**

1. አካል ጉዳተኝነት ተፈጥሯዊ የአካል መዛባት ነው።
2. ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል።
3. መምህራን አካል ጉዳተኞችን መረዳት አይችሉም።
4. የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች ጉዳት ከሌለባቸው ተለይተው መማር አለባቸው።
5. ሕንጻ ሲሰራ አካል ጉዳተኞችን ማገናዘብ የለበትም።

**ክፍለጊዜ፡ ሦስት**

**ለ. በ"ሀ" ስር ለቀረቡት ቃላት አውዳዊ ፍቻቸውን በ"ለ" ስር ከሚገኙት በመለየት አዛምዱ።**

| <u>ሀ</u> | <u>ለ</u> |
|---|---|
| 1. ያገናዘበ | ሀ. የረጅም ጊዜ |
| 2. ዘለቄታዊ | ለ. ከግምት ያስገባ |
| 3. ማመቻቸት | ሐ. ሳይታሰብ፣ በድንገት |
| 4. መዛባት | መ. ያልተስተካከለ መሆን |
| 5. አጋጣሚ | ሠ. ሁኔታዎችን ማስተካከል |
| 6. መረዳዳት | ረ. ያልታሰበ ጉዳት |
| 7. አደጋ | ሰ. መተጋገዝ፣ መደጋገፍ |

**ሐ. ከላይ በቀረበው በማዛመድ መልመጃ በ "ሀ" ረድፍ በቀረቡት ቃላት አረፍተነገር መስርታችሁ ለጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።**

**ክፍለጊዜ፡ አራት**

## መልመጃ ሁለት

**ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት መልሱ።**

1. አካል ጉዳተኛ ምንድን ነው?
2. የተወሰነ አካል ማጣት ሲባል ምን ማለት ነው?

3. የአካል ጉዳተኞች መብትን ከሌላው ማህበረሰብ ልዩ የሚያደርገው ምንድን ነው?
4. የተማሪዎች ልዩ ፍላጎት ማለት ምን ማለት ነው?
5. የአካል ጉዳተኝነት በአጋጣሚ የሚከሰተው እንዴት ነው?

**ክፍለጊዜ፡ አምስት**

ስታዳምጡ የያዛችኋቸውን አጫጭር ማስታወሻዎች በመገልገል አካል ጉዳተኞችን በተግባር እንዴት መርዳት እንዳለባችሁ ከቡድን አባላት ጋር ከተወያያችሁ በኋላ የደረሳችሁበትን ማጠቃለያ በጽሁፍ አደራጅታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንባብ አሰሙ።

**ክፍለጊዜ፡ ስድስት**

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር



### ተግባር አንድ

ከላይ የቀረበውን ስዕል እያያችሁ የአካል ጉዳተኝነት አይነቶችን፣ በምን ምክንያት ሊከሰቱ እንደሚችሉ፣ ጉዳቱ ያጋጠማቸውን እንዴት መርዳት እንደሚቻልና እንዴትስ አካል ጉዳተኝነትን መቀነስ እንደሚቻል በቡድን ሆናችሁ ተወያዩ።

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**

### ተግባር ሁለት

ሰዎችን በመጠየቅ በአካባቢያችሁ ያሉ የአካል ጉዳተኞችን በተመለከተ መረጃ ሰብስቡ። መረጃችሁ የአካል ጉዳታቸውን አይነትና ከማህበረሰቡ ድጋፍ ይደረግላቸው እንደሆነ የሚለይ ይሁን። የሰበሰባችሁትን መረጃ በማጠናከር ክፍል ውስጥ የቃል ዘገባ አቅርቡ።

**ክፍለጊዜ፡ ስምንት**

# ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

## ምንባብ አንድ

**የሚከተለውን ምንባብ ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ በመካከለኛ ፍጥነት አንቀፆቹን በጥንድ በጥንድ ተከፋፍላችሁ አንብቡ።**

መገርቱና ፍራኦል እህትና ወንድም ናቸው። ትምህርት ቤትም ሆነ ከትምህርት ቤት ሲመለሱ አብዛኛውን ጊዜያቸውን

የሚያሳልፉት አብረው ነው። የቤት ስራዎቻቸውንና ጥናታቸውንም አብረው ያከናውናሉ። ይህ መተጋገዛቸውም በትምህርታቸው አመርቂ ውጤት እንዲያስመዘግቡ አስችሏቸዋል። ብዙ ተማሪዎችም “እንደነሱ በርትተን ብናጠና ኖሮ ደረጃችንን ከፍ ማድረግ እንችል ነበር” ብለው ይቆጫሉ።

መገርቱና ፍራኦል በትምህርታቸው ከመተጋገዛቸው በተጨማሪ አንዳንዴም ቤተሰቦቻቸውን በአቅማቸው ስራ ያግዛሉ። ለምሳሌ ፍራኦል ለወላጆቹ ቡና ሲያፈላና ቁርስ ሲያዘጋጅ፣ መገርቱ ደግሞ አልጋ ታነጥፋለች። ፍራኦል ውሃ ለመቅዳት ሲሄድ፣ እሷ ደግሞ ሱቅ ትላካለች። እንዳንዴ ይህንኑ ስራቸውን እየተቀያየሩም ይሰራሉ። በስራ ድልድል ወቅት ይህ የሴት ያ የወንድ የሚባል ስራ እንደሌለም አምነው ተቀብለዋል። በትምህርታቸው ጎበዝ ስለሆኑና ወላጆቻቸውን እንደአቅማቸው ስራ የሚያግዙ በመሆናቸው ብዙ ሰው ያደንቃቸዋል።

መገርቱና ፍራኦል ነገሮችን መቼ፣ እንዴት፣ ለምን እንደሚከውኑ አስቀድመው ስለሚያውቁ ጊዜያቸውን አላግባብ አያባክኑም።

ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ

# ምንባብ ሁለት

## መረዳዳት

### ቅድመማንበብ ጥያቄዎች

1. ሰዎች እርስ በርሳቸው እንዴት ይረዳዳሉ?
2. ለአካል ጉዳተኞች ድጋፍ አድርጋችሁ ታውቃላችሁ?
3. የሚከተሉት ቃላት የያዙትን ፍች ገምቱ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| አሳሰበው፣ | ትብብር፣ | መቀጣጠር፣ | ዊልቸር |



እነቡልቻ በሚማሩበት ትምህርት ቤት የሚማሩ የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች አሉ። የተወሰኑት የአካል ጉዳታቸው መጠነኛ ሲሆን፣ ሌሎቹ ደግሞ በየእለቱ የሰው እገዛ የሚያስፈልጋቸው ናቸው። ከእነዚህ መካከል በዊልቸር የምትገፋው ሰላማዊትና ሁለቱ አይነስውራን ተማሪዎች ይጠቀሳሉ። ቡልቻ በበኩሉ ከዚህ ቀደም የተወሰነ እገዛ ለእነዚህ ተማሪዎች ሲያደርግላቸው ነበር። ይሁን እንጂ ብቻውን ሊወጣው ስለማይችል ጉዳዩ አሳስቦታል። ስለሆነም ይህንን ጉዳይ ለጓደኞቹ በማካፈል ትብብራቸውን ለመጠየቅ ወሰኗል። ጓደኞቹ እንደማያሳፍሩትም ተስፋ አድርጓል።

| |
|---|
| 1. ቡልቻ ሀሳቡ ይሳካለታል ብላችሁ ታስባላችሁ? |

**ቡልቻ፡** እኔ አንድ ሀሳብ አለኝ። እንደምናውቀው በትምህርት ቤታችን የኛን እገዛ የሚፈልጉ የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች አሉ። ለምን አንረዳቸውም?

**ጫልቱ፡** በትክክል ለምሳሌ በቀደምለት አይነስውሩ ልጅ መፅሐፍ የሚያነብለት ሰው አጥቶ ሲቸገር አይቼዋለሁ። ለመርዳት ባስብም ክፍለጊዜ ስለነበረኝ አልቻልኩም። ነገርግን እንደማነብለት ነግሬው ተቀጣጥረናል።

| |
|---|
| 2. ጫልቱ መፅሐፍ ልታነብለት ከአይነስውሩ ልጅ ጋር ____። |

**መገርቱ፡** በጣም ጥሩ ሀሳብ ነው። እኔ በበኩሌ ለመተባበር ዝግጁ ነኝ።

**ተክሌ፡** እኔ ፈቃደኛ ነኝ፤ እዚህ ትምህርት ቤት ሁለት አይነስውር ተማሪዎች አሉ፤ ሌላም በዊልቼር እየተገፋች የምትመጣ ተማሪ አለች። ዊልቸሩን የሚገፉላት ሰው ስለምታጣ ብዙ ጊዜ ትምህርት ቤት ትቀራለች።

| |
|---|
| 3. እኔ በበኩሌ ለመተባበር ዝግጁ ነኝ ያለችው _________ናት። |

**ጫልቱ፡** ስለዚህ ለትምህርት ቤቱ እናሳውቅና ተራ በተራ እየተረዳዳን ብናግዛቸው ጥሩ ይመስለኛል።

**መገርቱ፡** እንዲያውም የእረፍት ሰዓታችን ስለሆነ አሁኑኑ እናግኛቸው። ከዚያ እቅድ እናወጣና ተራ በተራ እንተጋገዛለን።

**ተክሌ፡**ይሆናል፤ አይነስውራኑን የተማርነውን በቃል እንከልስላቸዋለን፤ የሚያስፈልገውን ማጣቀሻ መፅሐፍ እናነብላቸዋለን እኛም በዚያው አጠናን ማለት አይደል?! ለባለዊልቸሯ ደግሞ ከሰፈሯ ስትመጣና ወደ ቤቷ ስትመለስ አብረን እየተጫወትን ዊልቸሯን እንገፋላታለን።

**ጫልቱ፡** ልክ ነህ መንገዳችን ተመሳሳይ ስለሆነ አንቸገርም። ማንበቡንም ቢሆን በተራ ስለምናደርገው ፈፅሞ አያሳስብም!

ቡልቻ፡ በጣም ጥሩ ውድ ጓደኞቼ! ሀሳቤን ተቀብላችሁ ዝግጁነታችሁን ስላሳያችሁኝ አመሰግናለሁ። ስለዚህ ልጆቹን እናግኛቸውና ፈቃደኝነታቸውን ጠይቀን ስራችንን ከዛሬው እንጀምር። ከዚያም ወደ ዳይሬክተራችን ቢሮ እንሄዳለን።

**ክፍለጊዜ፡ አስር**

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሶስት

**ሀ. በምንባቡ መሰረት ትክክል የሆነውን "እውነት" ያልሆነውን ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ።**

1. እነቡልቻ በሚማሩበት ትምህርት ቤት የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች የሉም።
2. ቡልቻ ያሳሰበውን ጉዳይ ለመፍታት ለጓደኞቹ በማካፈል ትብብራቸውን ጠየቃል።
3. አይነስውሩ ልጅ የተቸገረው መፅሐፍ የሚያነብለት ሰው አጥቶ ነው።
4. በዊልቼር እየተገፋ የሚመጣው ወንድ ተማሪ ሲሆን የቡልቻ ጓደኛ ነው።
5. ቡልቻና ጓደኞቹ ሊያደርጉ ያሰቡትን ድጋፍ ለትምህርት ቤታቸው ያሳውቃሉ።

**ለ. በ "ሀ" ስር ያሉትን ቃላት በ"ለ" ስር ካሉ ፍቺ ዎቻቸው ጋር አዛምዱ።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. አሳሰበው | ሀ. የአካል ጉዳተኞች ከአንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ የሚንቀሳቀሱበት |
| 2. መቀጣጠር | ለ. በምሳሌነት ይነሳሉ |
| 3. ዊልቸር | ሐ. በአይን ለማየት የሚቸገሩ |
| 4. ይጠቀሳሉ | መ. መተባበር፣ መተጋገዝ |
| 5. አይነስውር | ሠ. መልሶ ማየት |
| 6. መረዳዳት | ረ. ጉዳዩ አስጨነቀው |
| 7. መከለስ | ሰ. ለመገናኘት ማቀድ |

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ**

## መልመጃ አራት

**ሀ. በምንባቡ መሰረት ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ።**

1. እነቡልቻ በአካሄዱት ምክክር ላይ ያልነበረው ወይም ያልነበረችው ማነው? ማን ናት?

   ሀ. ጫልቱ    ለ. በለጠ    ሐ. ተክሌ    መ. መገርቱ

2. ለባለ ዊልቸሯ ድጋፍ የሚያደርጉላት፡-

   ሀ. በትምህርት ቤቱ ውስጥ

ለ. ከቤቷ ስትመጣና ወደቤቷ ስትሄድ

ሐ. በላይብረሪ ውስጥ ሆነው በማንበብ

መ. በሆስፒታል ውስጥ ስትታከም

3. "እኛም በዚያው አጠናን ማለት አይደል..." ያለው ማን ነው?

ሀ. ቡልቻ ለ. ጫልቱ ሐ. ሰናይት መ. ተክሌ

4. እነቡልቻ በእረፍት ጊዜያቸው ወዴት መሄድ አሰቡ?

ሀ. አካል ጉዳተኛ የሆኑትን ለማናገር

ለ. ባለዊልቸሯን ለመግፋት

ሐ. የቤት ስራቸውን ለመስራት

መ. 'ሀ' እና 'ለ' መልስ ይሆናሉ።

5. ቡልቻ ለብቻው ሊወጣው ያልቻለው ጉዳይ ምንድን ነው?

ሀ. አካል ጉዳተኞቹን መርዳት

ለ. የትምህርት ቤቱን ክፍያ

ሐ. ለፈተና መዘጋጀቱን

መ. ዳሬክተራችን ቢሮ መሄዱን

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት**

**ለ. ቀጣዮቹን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃል መልሱ።**

1. ከላይ የቀረበውን ታሪክ ባጭሩ ለጓደኞቻችሁ በቃል ንገሩ።

2. የታሪኩ ዋና መልዕክት ወይም ጭብጥ ምንድን ነው?
3. በትምህርት ቤታችሁ ተመሳሳይ ችግር ቢያጋጥም እናንተ ምን ታደርጉ ነበር?

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሦስት**

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

**ማስታወሻ**

ቅጥያዎች በቃል መጀመሪያ ወይም በቃል መጨረሻ ላይ ሊቀጠሉ ይችላሉ።

ምሳሌ፡ የልጅ = የ- ልጅ ተጠራ = ተ- ጠራ

ሀገሮች = ሀገር-ኦች ሰውነት = ሰው - ነት

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት**

### መልመጃ አምስት

**ሀ. በሚከተሉት ቃላት ውስጥ ያሉ ቅጥያዎችን ለዩ።**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሰማያዊ | አስመለሰ | አልመጣም | ፈረሰኛ |
| ጠራው | ሂደች | ተወረወረ | አስመጣ |
| ቅጥያዎች | | | |

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት

ለ. ተከታዮቹን ቅጥያ ያላቸው ቃላት ተጠቅማችሁ ዓረፍተነገር መስርቱ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች | እነዮሐንስ | በሬው | መረዳዳታችን |
| መጫወቻዬ | እንተባበር | አምጪው | የደራርቱ |

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት

### መልመጃ ስድስት

የሚከተሉትን አረፍተነገሮች ደብተራችሁ ላይ ፃፉና ቅጥያ ያለባቸውን ቃላት በሙሉ አስምሩባቸው።

1. ትዕግስት ስለመጣች ደስ አለኝ።
2. ሮባ ብዙ ደብተሮች ይገዛል።
3. ተራራማ አካባቢዎችን አየሁ።
4. እነማሞ ወደቤት እየሄዱ ነው።
5. ሁለት ብርጭቆዎች ተሰበሩ።
6. የሰለሞን ወንድም በሬዎቹን አሰማራ።
7. እርሳስ፣ መቅረጫ እና ደብተሮች ገዛሁ።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት

**ማስታወሻ**

**ድርብ አረፍተነገሮች** በውስጣቸው ሁለት ራሳቸውን የቻሉ ሀረጎች አሏቸው።

**ምሳሌ፡** እሷ መጣች። እሷ ሰላምታ አቀረበች።

እሷ መጣችና ሰላምታ አቀረበች።

**ድብልቅ አረፍተነገሮች** አንድና ከአንድ በላይ ጥገኛ ሀረግና አንድ ራሱን የቻለ ሀረግ አላቸው።

ምሳሌ፡ እናታችን ገበያ ሄደች።

አባታችን ቁርስ አዘጋጅቶ አቀረበልን።

እናታችን ገበያ ስትሄድ አባታችን ቁርስ አዘጋጅቶ አቀረበልን።

## መልመጃ ሰባት

**በማስታወሻው መሰረት የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች ድርብ ወይም ድብልቅ ዓረፍተነገር በማለት ለዩ።**

1. አስቴር ቁርሷን በልታ ትምህርት ቤት ሄደች።
2. ዱላ ጥናቱን በአግባቡ አካሂዷል፤ ፈተናውን አልፏል።
3. ትጉህ ልጆች የጊዜን ጥቅም ያውቃሉ፤ ጊዜን

ባግባቡ ይጠቀማሉ።

4. መምህራችን ቤተሰቧን ልትጠይቅ ስትሄድ፣ እኛ ቤተመጽሃፍት ሄደን አጠናን።
5. የበጋው ወቅት ስለመጣ ሙቀቱን ለመቋቋም ሰዎች ዣንጥላ ይይዛሉ።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

## መልመጃ ስምንት

**ከዚህ በታች የቀረቡላችሁን አረፍተነገሮች ድርብ ወይም ድብልቅ እያላችሁ ለዩአቸው።**

1. ቡድኑ ጠንክሮ በመጫወቱ ጨዋታውን አሸንፎ ዋንጫውን ወሰደ።
2. አቶ ቶሊ እና ወይዘሮ አልማዝ ከተጋቡ ቆይተዋል፤ በትዳራቸውም አራት ልጆች አፍርተዋል።
3. ልጆች መጫወት ቢኖርባቸውም መጫወቻ ስፍራዎችን ግን መምረጥ ይገባቸዋል።
4. ፋጡማ ከትምህርት ቤት መጣችና የቤት ስራዎቿን ወዲያው ሰራች።

## ተግባር አራት

**በየግላችሁ አምስት ድርብ እና አምስት ድብልቅ አረፍተነገሮችን በመፃፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።**

# ምዕራፍ አራት፡ ሥርዓተጸታ

ክፍለጊዜ፡ አንድ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

በዚህ ትምህርት ስር የማዳመጥ ክሂላችሁን እንድታሻሽሉ የሚረዱ የተለያዩ መልመጃዎችና ተግባራት ስለቀረቡ በትእዛዛቱ መሰረት በትኩረት ስሩ።

### የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

1. እቤታችሁ ምን ስራ በመስራት ወላጆቻችሁን ታግዛላችሁ?
2. ከእህቶቻችሁ ወይም ከወንድሞቻችሁ ጋር የምትሰሯቸው ተመሳሳይ ስራዎችን ዘርዝሩ።
3. ከእህቶቻችሁ ወይም ከወንድሞቻችሁ ጋር የምትሰሯቸው የተለዩ ስራዎችን ዘርዝሩ።

### የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. የጋዲሴ ወንድም ስም ----------ይባላል።
2. ጋዲሴ የምትኖረው ከ--------፣ከ--------፣ ከ--------፣ እና ከ------- ጋር ነው።

**ክፍለጊዜ፡ ሁለት**

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

1. በአዳመጣችሁት ጽሁፍ መሰረት በቡድናችሁ ተወያይታችሁበት የተስማማችሁበትን መልስ በሚከተለው ሰንጠረዥ ውስጥ አሟሉ።

| | የጋዴሴ ስራዎች | የጉዲሳ ስራዎች |
|---|---|---|
| 1 | እናቴ ምግብ ስታበስል<br>እቃ በማቀራረብ ማገዝ | ልብስ ማጠብ |
| 2 | | |
| 3 | | |

**ክፍለጊዜ፡ ሶስት**

2. ጋዲሴን ቅር የሚያሰኟትን ጉዳዮች ለጓደኞቻችሁ በቃል ተናገሩ።
3. የጋዲሴ እና የጉዲሳ የስራ ክፍፍል ፍትሃዊ ነው ብላችሁ ታስባላችሁ? ፍትሃዊ ካልሆነ ለምን?
4. ጋዲሴ እንደወንድሟ ውጪ ወጥታ ከጓደኞቿ ጋር እንዳትጫወት እና እንዳታነብ ቤተሰቦቿ የሚቆጣጠሯት ለምን ይመስላችኋል?

**ክፍለጊዜ፡ አራት**

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

## ተግባር አንድ

**ሀ. በአዳመጣችሁት ጽሁፍ መሰረት ከዚህ በታች የተዘረዘሩ የጋዲሴ እና የጉዲሳ ስራዎች ተገቢ ናቸው ወይም አይደለም በሚል አቋም ይዛችሁ ተከራከሩ።**

1. ጉዲሳ እናቱን እቃ በማቀራረብ መርዳት

   አለበት/የለበትም።

2. ጋዲሴ እንደወንድሟ ከጓደኞቿ ጋር መጫወት

   አለባት/የለባትም።

**ክፍለጊዜ፡ አምስት**

**ለ. በአካባቢያችሁ ከምትገነዘቡት የወንዶችና የሴቶች የስራ ክፍፍል ሁኔታን በተመለከተ መረጃ ከሰበሰባችሁ በኋላ መረጃውን አደራጅታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል ንግግር አድርጉ፡፡**

## ክፍለጊዜ፡ ስድስት

**ማስታወሻ**

ክርክር በመረጃ አስደግፎ የራስን ሀሳብ በማቅረብ የተቃራኒ ቡድንን ሀሳብ ደግሞ ለማሸነፍ የሚደረግ የሀሳብ ፍጭት ሂደት ነው።

**ለክርክር የሚደረግ ቅድመ ዝግጅት**

1. የመከራከሪያ ርዕሶቹን መረዳት
2. የራስን ርዕስ የሚደግፍና የተቃራኒ ሀሳብ የሚያፈርስ ሀሳብ ማመንጨት
3. በርዕሱ ዙሪያ በመጠየቅ በማንበብ ዝግጅት ማድረግ
4. ተቃራኒ ቡድን ሲያቀርቡ አዳምጦ የተሻለ ሀሳብ ማቅረብ

**ክርክር በሚደረግበት ጊዜ መደረግ ያለባቸው ነገሮች**

1. የክርክሩን ርዕስ ማስተዋወቅ
2. ፍርሃትን ማስወገድ እና ሀሳብን በቅልጥፍና ማቅረብ
3. ሀሳብን አለመደጋገም
4. የተቃራኒን ሀሳብ በደንብ በማዳመጥ ለክርክሩ የተሰጠውን ጊዜ በአግባቡ መፈጸም

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**

# ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ



## ቅድመማንበብ ጥያቄዎች

1. ከምስሉ የተረዳችሁትን ለመምህራችሁ ንገሩ።
2. በቤተሰባችሁ የስራ ድርሻ የሚያከፋፍላችሁ ማን ነው?
3. ወላጆቻችሁ የሚያዟችሁን ስራዎች ሁሉ ትሰራላችሁ?

## የቤተሰብ አባላት የስራ ድርሻ

በሁሉም ቤተሰብ የቤተሰቡ አባላት የስራ ድርሻን የሚከፋፈሉት በተመሳሳይ ሁኔታ አይደለም። እያንዳንዱ ቤተሰብ ስራን የሚከፋፈሉበት የራሳቸው መንገድ አላቸው። በአብዛኛው

ቤተሰብ የቤተሰብ አባላትን ግዴታ፣ መብት እና የስራ ድርሻ የሚመድቡት ወላጆች ናቸው።

አንድ ጊዜ ወላጆች የስራ ድርሻ እና ኃላፊነትን ከወሰኑ በኋላ ከልጆች የሚጠበቀው ይህንን ውሳኔ ተከትለው መተግበር ነው። ነገርግን ልጆች እያደጉ ሲመጡ ራሳቸውን ለመምራት ጥያቄ ያቀርባሉ። በተጨማሪም ፍላጎታቸው እና የግል አመለካከታቸው ትኩረት እንዲሰጠው ይጥራሉ። ቢሆንም ብዙውን ጊዜ የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጡ ወላጆች ናቸው።

1. እስከአሁን ከአነበባችኋቸው አንቀፆች ስለቤተሰብ አባላት የስራ ክፍፍል ምን ተረዳችሁ?

ከዚህ ጋር በተያያዘ በቤተሰብ ዘንድ ከእድሜ ታላቅነትና ታናሽነት ጋር የተያያዘ ተዋረዳዊ የስራ ድርሻ ክፍፍል የተለመደ ሲሆን አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ከስርዓተጾታ ጉዳዮች ጋር የሚያያዝበት አጋጣሚ አለ። ለምሳሌ በኢትዮጵያ አውድ በተለምዶ ወንዶች ከሴቶች የበለጠ የመወሰን አቅም አላቸው ይባላል። ከዚህ አኳያ አባት ለቤተሰቡ የሚያስፈልጉ ነገሮችን አቅራቢ፣ የቤተሰቡ ምሰሶ እና የመጨረሻ ውሳኔ ሰጪ አካል ተደርጎ ይታሰባል። ቢሆንም ከእናቶች አንጻር ሲታይ አባቶች በቤተሰቡ ውስጥ ያላቸው ተግባር ውስን ሆኖ እናገኘዋለን።

እናቶች የቤተሰቡ ተንከባካቢዎች ሲሆኑ ቤተሰቡ የሚያስፈልገው ነገሮች በማሟላት ረገድ ኃላፊነታቸው ጉልህ ነው። እናቶች የቤተሰቡን አባላት ህብረት እንዲጠናከር ማድረግ እና ግንኙነታቸውም ሰላማዊ እንዲሆን የሚያበረክቱት አስተዋጽዖ ከፍተኛ ነው። ይህም እናቶች እና አባቶች በቤተሰብ ውስጥ የተለያየ የስራ ኃላፊነት እንዳላቸው ያመለክታል።

2. ተለምዷዊ የቤተሰብ አባላት የስራ ድርሻ ክፍፍል ሁኔታን አብራሩ።

በአሁን ጌዜ ግን አባቶች እና እናቶች ቤተሰቡን ገቢ በማምጣት ስለሚሳተፉ ተለምዷዊው ጾታ ተኮር መዋቅር ተግዳሮት እየገጠመው ይገኛል። ነገርግን አሁንም ድረስ ሴቶች የቤት ውስጥ እና የቢሮ ስራዎችን አጣምረው የመስራት ኃላፊነትን እየተወጡ እንደሚገኙ በገሃድ የሚታይ እውነታ ነው። አንዳንድ አባቶች ህጻናትን የመንከባከብ ኃላፊነትን የሚወጡ ቢኖሩም አብዛኛቹ አባቶች ግን ህጻናትን መንከባከብ እና የቤት ውስጥ ስራዎች የሴቶች ድርሻ እንደሆነ ይቆጥራሉ።

3. የአሁን ጊዜ ቤተሰብ የስራ ድርሻ ክፍፍል ሁኔታ ምን ይመስላል?

ከዚህ አንጻር ደስተኛ ቤተሰብ ለመፍጠር ሁሉንም የቤተሰብ አባላት ባሳተፈ ሁኔታ በመወያየት እና በመመካከር የቤተሰቡን የስራ ድርሻዎች መከፋፈል ያስፈልጋል።

**ክፍለጊዜ፡ ስምንት**

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

**ሀ. የሚከተሉትን ሀሳቦች በምንባቡ መሰረት “እውነት” ወይም “ሀሰት” በማለት በቃል መልሱ።**

1. የቤተሰብ አባላት የስራ ድርሻን የሚከፋፈሉት በተመሳሳይ ሁኔታ ነው።
2. የቤተሰብ አባላትን ግዴታ፣ መብት እና የስራ ድርሻ የሚመድቡት ልጆች ናቸው።
3. ልጆች እያደጉ ሲመጡ ራሳቸውን ለመምራት ጥያቄ ያቀርባሉ።
4. በቤተሰብ ብዙውን ጊዜ የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጡ ወላጆች ናቸው።
5. በኢትዮጵያ አውድ በተለምዶ ሴቶች ከወንዶች የበለጠ የመወሰን አቅም አላቸው ይባላል።
6. ከእናቶች አንጻር ሲታይ አባቶች በቤተሰቡ ውስጥ ያላቸው ተግባር ጉልህ ሆኖ እናገኘዋለን።

7. በአሁን ጊዜ የቤተሰብን ገቢ በማምጣት አባቶች እና እናቶች ይሳተፋሉ።
8. በአሁን ጊዜ ህጻናትን የመንከባከብ ኃላፊነትን የሚወጡ አንዳንድ አባቶች አሉ።
9. ደስተኛ ቤተሰብ ለመፍጠር ሁሉም የቤተሰብ አባላት መመካከር አለባቸው።

**ክፍለጊዜ ዘጠኝ**

**ለ. የሚከተለውን ሰንጠረዥ በምንባቡ መሰረት አሟሉ**

| ተራ ቁጥር | ተለምዷዊ የወላጆች ኃላፊነት | የአሁን ጌዜ የወላጆች ኃላፊነት |
|---|---|---|
| 1 | ለወንዶች ከሴቶች የበለጠ የመወሰን መብት ይሰጣል፤ | ሴቶች እና ወንዶች የቤተሰቡን ገቢ በማምጣት ይሳተፋሉ፤ |
| 2 | | |
| 3 | | |

**ክፍለጊዜ፡ አስር**

**ሐ. በ "ሀ" ስር ለቀረቡት አንቀጾች በ "ለ" ከቀረቡት ጭብጦቻቸው ጋር አዛምዱ።**

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. አንቀጽ አንድ | ሀ. ልጆች ሲያድጉ የሚሰማቸው ኃላፊነት የመቀበል ስሜት |
| 2. አንቀጽ ሁለት | ለ. የስራ ድርሻ የማከፋፈል ኃላፊነት የተሰጣቸው አካላት |
| 3. አንቀጽ ሶስት | ሐ. ዘመናዊ የስራ ድርሻ |

| | |
|---|---|
| | ኃላፊነት አወሳሰድ |
| 4. አንቀጽ አራት | መ. ስለደስተኛ ቤተሰብ አመሰራረት |
| 5. አንቀጽ አምስት | ሠ. ተለምዷዊ የስራ ድርሻ ኃላፊነት አወሳሰድ |

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ**

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

የውሰት ቃላት የሚባሉት አንድ ቋንቋ የሌለውን ቃላት ከሌላ ቋንቋ በመውሰድ የሚጠቀማቸው ቃላት ናቸው።እነዚህም የተለያዩ ቋንቋዎች ከሚናገሩ ህብረተሰቦች ትስስር ምክንያት የሚፈጠሩ ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ ቴክኖሎጂ የፈጠራቸው ነገሮች በቀጥታ ስማቸውን ይዘው ስለሚመጡ እንዳለ በመዋስ ይጠቀማል።

ምሳሌ፡ አማርኛ እና አፋን ኦሮሞ ስለሚቀራረቡ አማርኛ ከአፋን ኦሮሞ የወሰዳቸውን ቃላት እንመልከት

ሰንጋ፣ ጮማ፣ ጉዲፈቻ፣ ጨጨብሳ ወዘተ አማርኛ ከአፋን ኦሮሞ በተውሶ የወሰዳችው ናቸው።

አማርኛ ከውጭ ቋንቋዎች ብዙ ቃላት ወስዷል።

ለምሳሌ፡ ኮምፒውተር፣ ፌስቡክ፣ ሞተር፣ ዋይፋይ፣ ሪሞት፣ ሸሚዝ፣ ጀበና ወዘተ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት**

## መልመጃ ሶስት

ሀ. ከሚከተሉት የተውሶ ቃላት የሆኑትን ለዩ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሞፈር | ገበሬ | መሶብ | ሚዲያ |
| ቤት | ሰው | ቴሌቪዥን | አትሌት |

ለ. በቴክኖሎጂ ምክንያት ወደ አማርኛ ቋንቋ የገቡ ሀያ ቃላትን ጻፉ።

ምሳሌ፡ ቪዲዮ፣ ሲም ካርድ…

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሶስት**

## መልመጃ አራት

ሀ. በሚከተለው ሠንጠረዥ የተዘረዘሩት ቃላት የተውሶ ወይም የተውሶ ያልሆኑ በማለት ከፊት ለፊታቸው በመጻፍ ለዩ።


| ተ.ቁ | ቃል | የተውሶ ቃል | የተውሶ ያልሆነ |
|---|---|---|---|
| 1 | ገበታ | | |
| 2 | ሞባይል | | |
| 3 | ሬድዮ | | |
| 4 | ገበቴ | | |
| 5 | መንገድ | | |
| 6 | ሶላር | | |

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት


ለ. ከላይ ከተሰጣችሁ ሌላ የተውሶ ቃላትን ቢያንስ አምስት በመጻፍ ለመምህራችሁ አሳዩ።

ሐ. የሚከተለውን አሟልታችሁ ጻፉ።

ከአፋን ኦሮሞ
ወደ አማርኛ ቋንቋ
የገቡ የውሰት ቃላት




በቴክኖሎጂ ምክንያት
ከሌሎች የውጭ ሀገር
ቋንቋዎች ወደ አማርኛ
ቋንቋ የገቡ የውሰት ቃላት



## ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋሰው

**ማስታወሻ**

ከአማርኛ የቃል ክፍሎች አንዱ ግስ ነው። ግስ ድርጊትን የሚያመለክት ነው። ለምሳሌ፡ “ሞሲሳ ዳቦ በላ” ከነዚህ ሶስት ቃላት ግስ የሚሆነው “በላ” ነው። ምክንያቱም በዓረፍተነገሩ ውስጥ የተፈጸመው ድርጊት “መብላት” በመሆኑ ነው። ከዚህ አንጻር ድርጊት ፈጻሚው “ሞሲሳ” ሲሆን ድርጊት የተፈጸመበት ደግሞ “ዳቦ” ነው።

## መልመጃ አምስት

**ሀ. ከሚከተሉት ቃላት ግስ የሆኑትን ለይታችሁ ጻፉ።**

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ሮጠ | ጻፈ | ሩጫ | አጠረ | አጥር | እርሻ |
| ጽህፈት | አጨደ | አጨዳ | ገመደ | አረሰ | ገመድ |

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት

**ለ. ከሚከተሉት አረፍተነገሮች ግስ የሆኑትን ለዩ።**

1. የዝሆን ሎተሪ እጣ ወጣ።
2. ቶሌራ መረብ ኳስ ተጫወተ።
3. ጓደኛዬ አጥሩን ዘለለ።

4. ቤታቸው በመንገድ ልማት ሰበብ ፈረሰ።

5. ቶልቱ ፈረስ ጋለበች።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት**

**ሐ. በሚከተለው ሠንጠረዥ በቀረቡትን ቃላት ትይዩ ግሶች ናቸው ወይም ግሶች አ ይደሉም በማለት ጻፉ።**

| ተ.ቁ | ቃል | ግስ | ስም |
|---|---|---|---|
| 1 | በቀለ | | |
| 2 | ተክል | | |
| 3 | በሬ | | |
| 4 | ቀዳ | | |
| 5 | ፀለየ | | |
| 6 | ፀሎት | | |
| 7 | ፈጠነ | | |
| 8 | ፍጥነት | | |
| 9 | ሣር | | |
| 10 | አሠረ | | |

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት

መ. በምሳሌው መሰረት በሚከተሉት ግሶች ባለቤቱን እና ማሰሪያ አንቀጹ በሴት ጾታ እያስማማችሁ ዓረፍተነገር ሥሩ።

| |
|---|
| ምሳሌ፡ አሰረ ገመዱ በሬውን ግንዱ ላይ አሰረች። "አሠረች" ግስ ወይም "ማሰሪያ አንቀጽ" ነው።<br>ያለ ግስ ዓረፍተነገር አያልቅም። |

1. ቀለጠ
2. አመነ
3. ዘመረ
4. ደወለ

# ምዕራፍ አምስት፡ ጉብኝት

**ክፍለጊዜ፡ አንድ**

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

**በዚህ ትምህርት ክፍል የሚነበብላችሁ ጽሁፍ አዳምጣችሁ የምትሰሯቸው መልመጃዎች ስለቀረቡ በትእዛዛቱ መሰረት መልሱ።**





## ቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ስዕሉ ከሀገራችን የቱሪስት መስህብ መዳረሻ ስፍራዎች የትኞቹ ናቸው?
2. በአካባቢያችሁ ሊጎበኙ የሚችሉ ስፍራዎች አሉ?

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. የተራኪው እና የቤተሰቦቹ የጉዞ መነሻ----------ነው።
2. የተጓገሮቹ መድረሻ -----------ነው።
3. ሶፍዑመር ዋሻ --------ክልል ይገኛል።
4. ተጓገሮቹ ቁርስ የበሉት ------ከተማ ነው።
5. ብዙ ብርቅዬ አራዊቶች የሚገኙት በ ------ ውስጥ ነው።
6. በሶፍዑመር ዋሻ ውስጥ የሚገኘው ወንዝ ስም-----ነው።

**ክፍለ ጊዜ፡ ሁለት**

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

## መልመጃ አንድ

**ሀ. የሚከተሉትን ሃሳቦች “እውነት” ወይም “ሀሰት” በማለት በቃል መልሱ።**

1. እኔ እያለ የሚናገረው ሰው ማን እንደሆነ ይታወቃል።
2. ጉዞው የተጀመረው ከቢሾፍቱ ከተማ ነው።

3. ሶፍ ዑመር ዋሻ የሚገኘው በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን ነው።
4. በጉዟቸው ከሶፍ ዑመር ሌላ ዋሻ አግኝተዋል።
5. ቆሎ ገዝተው የቆረጠሙት ለቁርሳቸው ባቱ ከተማ ነው።
6. የሶፍ ዑመር ዋሻ ዋና መግቢያ በር አዮመኮ ይባላል።
7. በዋሻው ውስጥ ሐይቅ እንጂ ወንዝ የለም።
8. በባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክን ሲያልፉ የተመለከቱት እንስሳ ዝሆን ነበር።
9. "እኔ" የሚለው ሰው የሄደው ከመስሪያ ቤት ጓደኞቹ ጋር ነው።
10. ከዲንሾ ወደሮቤ ሲጓዙ ግራቀኝ ያዩት የሰንዴ እና የገብስ አዝመራ ነው።

**ለ. የሚከተሉት ጥያቄዎች ከ "ለ" ወደ "ሀ" በትክክለኛው መልስ አዛምዱ።**

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ገታ | ሀ. ያልተሠበሰበ እህል |
| 2. አዝመራ | ለ. በባሌ ፓርክ የሚገኝ እንስሳ |
| 3.እያማተርን | ሐ. ዋናው የሶፍ ዑመር መግቢያ |
| 4. ከርከሮ | መ. እየተመለከትን |
| 5. አዮመኮ | ሠ. ቆም |

**ክፍለጊዜ፡ ሶስት**

**ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ።**

1. የቤተሰቡ ጉዞ መዳረሻው የሚሆነው

   ሀ. ቢሾፍቱ ለ. ባቱ ሐ. አዳማ መ. ሶፍዑመር ዋሻ

2. በባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ ውስጥ የሚገኝ እንስሳ የቱ ነው?

   ሀ. ዝሆን ለ. አውራሪስ ሐ. ኒያላ መ. ቀጭኔ

3. ተጓዦቹ ቁርሳቸውን የበሉት

   ሀ. ባቱ ለ. ጎሮ ሐ. ዲንሾ መ. መልካ

4. ከአዮመኮ እስከ ሁለቃ ያለው የዋሻው ርዝመት

   ሀ. 20 ኪ.ሜ ለ.15.6 ኪ.ሜ ሐ. 30.4 ኪ.ሜ
   መ. ርቀቱ አይታወቅም

5. ተጓዦቹ የተጓዙት በምንድን ነው?

   ሀ. በፈረስ ለ. በባቡር ሐ. በአይሮፕላን መ. በመኪና

6. በባሌ ዲንሾ የተለመደው ቆሎ ከምንድነው የሚዘጋጀው?

   ሀ. ከስንዴ ለ. ከበቆሎ ሐ. ከገብስ መ. ከአጃ

7. ተጓዦች በመጨረሻ

   ሀ. ጉዞ ስለጎዳቸው ተጎሳቁለዋል
   ለ. ህብረተሰቡ አበሳጭቷቸዋል
   ሐ. በጣም ተደስተዋል
   መ. ሳይሳካላቸው ቀርተዋል

8. “ሰብስቤ ዋሻ” የተባለው የሚኖሩበት ሰዎች_ናቸው።

ሀ. የሰብስቤ ቤተሰቦች ሐ. ሀናለ

ለ. የአካባቢው ሰዎች መ. ሁሉም መልስ ይሆናል

**መ. ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. ተጓገሮቹ ስንት ዋሻዎች አዩ?
2. ባሌ ሮቤ ሳይደረስ ያገኙት ዋሻ ምን ተብሎ ይጠራል?
3. የሶፍዑመር ዋሻ ለምን የተፈጥሮ መስህብ ተባለ?
4. ከኒያላ ውጭ በባሌ ብሔራዊ ፓርክ የሚገኙ ሌሎች አራዊትን ዘርዝሩ።

**ክፍለጊዜ፡ አራት**

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### ተግባር አንድ

**ሀ. መስህብነት ያላቸው በአካባቢያችሁ የሚገኙ ቦታዎችን ጎብኝታችሁ የጉብኝታችሁን ዘገባ በቃል ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።**

**ክፍለጊዜ፡ አምስት**

**ለ. ቤተሰቦቻችሁ ከዚህ በፊት የጎበኟቸውን የቱሪስት መስህብ ያላቸውን ቦታዎች ጠይቃችሁ ማስታወሻ በመያዝ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ።**

ክፍለጊዜ: ስድስት

# ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ



## የቅድመማንበብ ጥያቄዎች

1. ስለምትመለከቱት ፎቶ የምታውቁትን ለመምህራችሁ ተናገሩ።
2. በአካባቢያችሁ ብዙ ዘመን ያስቆጠሩ ቤቶች ካሉ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።
3. ምንባቡን ስለምን ጉዳይ የሚያብራራ ይመስላችኋል?

## ጥንታዊ የጉብኝት መዳረሻዎች

ሶፊያ ያደገችው ሀረር ነው። አብዛኛው ጊዜዋን የምታሳልፈው በመጻፍ እና የቱሪስት መስህብ ስፍራዎችን በመጎብኘት ነው። በጉብኝቷ ወቅት ከተለያዩ ሰዎች ጋር የመተዋወቅ እድል አጋጥሟታል፤ እንዲሁም አዳዲስ ቦታዎችን እንድታውቅ

ረድቷታል። ከጎበኘቻቸው ውስጥ የአብዛኞቹን ስፍራዎች ፎቶግራፍ አሏት።

ዮርዳኖስ የምትኖረው ከሶፊያ መኖሪያ ቤት ቀጥሎ ነው። እሷም በኢትዮጵያ የሚገኙ ጥንታዊ የጉብኝት መዳረሻዎችን ለማወቅ ትፈልጋለች። ስለእነዚህ መዳረሻዎች ሶፊያን በመጠየቅ ለመረዳት ፈለገች። በዚህም ምክንያት ሶፊያን በማግኘት በሚከተለው መንገድ ጠይቃ ስለስፍራዎቹ ለመረዳት ጥረት አደረገች።

1. ዮርዳኖስ ሶፊያን ምን ምን እንደምትጠይቃት ገምቱ።

**ዮርዳኖስ፡** ጥንታዊ የጉብኝት መዳረሻዎች የቱሪስት መስህብ እንደሆኑ ሰምቻለሁ፤ ይህ ምን ያህል እውነት ነው?

**ሶፊያ፡** ትክክል ነው፤ ጥንታዊ የጉብኝት መዳረሻዎች ቱሪስቶች ለመጎብኘት ከሚፈልጓቸው ስፍራዎች ዋነኞቹ ናቸው።

**ዮርዳኖስ፡** በአገራችን የሚጎበኙ ጥንታዊ የጉብኝት መዳረሻዎች አሉ እንዴ?

**ሶፊያ፡** አዎ! አሉ። በአገራችን ብዙ ሊጎበኙ የሚገባቸው ጥንታዊ የጉብኝት መዳረሻዎች ይገኛሉ።

2. በአገራችን ጥንታዊ ስፍራዎች የት የት አካባቢ ይገኛል ብላችሁ ትገምታላችሁ?

**ዮርዳኖስ፡** እነዚህ ቦታዎች ምን ያህል አስፈላጊ ናቸው?

**ሶፊያ፡** ጥንታዊ የጉብኝት መዳረሻዎች የሀገራችንን ቀደምት ስልጣኔ እና ዕድገት ለማሳየት እንደ ማስረጃ የሚቀርቡ ናቸው። እንዲሁም የሀገሪቷን ታሪክ ማሳያዎች ናቸው።

**ዮርዳኖስ፡** እነዚህን የቱሪስት መስህቦች ጎብኝተሻል? ከጎበኘሽ ስለሀገራችን ጥንታዊ የጉብኝት መዳረሻዎች ምን ምን ልምዶች አሉሽ?

**ሶፍያ፡** በጣም ከሚታወቁ ጥንታዊ ስፍራዎች የተወሰኑትን ጎብኝቻለሁ። በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች የሚገኙ ጥንታዊ የጉብኝት መዳረሻዎች አውቃለሁ። እነዚህም ጎብኝዎችን የሚስቡ ታሪካዊ ስፍራዎች ናቸው።

**ዮርዳኖስ፡** ከእነዚህ መዳረሻዎች ስለአንዱ ልትነግሪኝ ትችያለሽ?

**ሶፍያ፡** በደንብ ነዋ! ባለፈ ሳምንት ከእነዚህ መዳረሻዎች መካከል አንዱን የመጎብኘት ዕድል አጋጥሞኝ ነበር። እስቲ ይህንን ፎቶ ተመልከቺ። ይህ የንጉስ አባጅፋር ቤተመንግስት ፎቶ ነው።

| |
|---|
| 3. የንጉስ አባጅፋር ቤተመንግስት የት የሚገኝ ይመስላችኋል? |

**ዮርዳኖስ፡** የት ነው የሚገኘው?

**ሶፍያ፡** በጅማ ከተማ።

**ዮርዳኖስ፡** አ! እንዴት የሚያምር ስፍራ ነው! ከዚህ በፊት አላውቀውም ነበር፤ ከዚህ በኋላ በአገኘሁት አጋጣሚ እንዲህ ያሉ ጥንታዊ የጉብኝት መዳረሻዎች ለመጎብኘት እሞክራለሁ።

**ክፍለጊዜ፡ ስድስት**

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

**ሀ. የሚከተሉትን ሃሳቦች በምንባቡ መሰረት “እውነት” ወይም “ሐሰት” በማለት በቃል መልሱ።**

1. ሶፊያ ያደገችው ድሬዳዋ ነው።
2. ሶፊያ አብዛኛው ጊዜዋን የምታሳልፈው በመጻፍ እና የቱሪስት መስህብ ስፍራዎችን በመጎብኘት ነው።
3. ዮርዳኖስ የምትኖረው ከሶፊያ መኖሪያ ቤት ቀጥሎ ነው።
4. ሶፊያ ስለጥንታዊ ስፍራዎች ለማወቅ ዮርዳኖስን ጠየቀች።
5. ጥንታዊ ቦታዎች የሀገራችንን ቀደምት ስልጣኔ እና ዕድገት ለማሳየት እንደ ማስረጃ የሚቀርቡ ናቸው።
6. “ጥንታዊ ስፍራዎችን ለመጎብኘት እሞክራለሁ።” ያለችው ሶፊያ ናት።

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**

**ለ. በ “ሀ” ስር ለሚገኙት ቃላት አገባባዊ ፍች ከ “ለ” በመምረጥ አዛምዱ።**

| “ሀ” | “ለ” |
|---|---|
| 1. ቱሪስት | ሀ. የጥንት |
| 2. መዳረሻዎች | ለ. ጎብኚ |
| 3. ቤተመንግስት | ሐ. ዘመናዊነት |
| 4. መስህብ | መ. የንጉሶች መኖሪያ |
| 5. ቀደምት | ሠ. አጓጊ |
| 6. ስልጣኔ | ረ. የጉብኝት ቦታዎች |

**ክፍለጊዜ፡ ስምንት**

## ተግባር ሁለት

**የሚከተለውን ሰንጠረዥ ሶፊያና ዮርዳኖስ በተጠቀሟቸው ጥያቄ እና መልስ አሟሉ። ስታሟሉ በቀጥታ ከምንባቡ አትውሰዱ፤ በራሳችሁ አገላለጽ እንድታሟሉ ይጠበቃል።**

| **የዮርዳኖስ ጥያቄዎች** | **የሶፊያ መልሶች** |
|---|---|
| የጉብኝት ቦታዎች አጓጊዎች ናቸው የሚባለው እውነት ነው? | አዎ! በርካታ ጎብኚዎች የሚስቡ ናቸው። |
| | |

ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

### ተግባር ሶስት

ሀ. "ጥንታዊ የጉብኝት መዳረሻዎች" በሚለው ምንባብ የተካተቱ ዋና ዋና ሀሳቦችን ለይታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

ክፍለጊዜ፡ አስር

ለ. ከዚህ በታች የሚገኘው አንቀጽ ዋና ሃሳብ ጽፋችሁ ለክፍል ተማሪዎች አንብቡ።

ባለፈው ሳምንት ቦንቱና የክፍል ጓደኞቿ በኦሮሚያ ክልል የሚገኙ የተለያዩ የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎችን ጎበኙ። በመጀመሪያ ባሌ ተጉዘው የባሌውን አስደናቂ የሶፍዑመር ዋሻ ጎበኙ። በመቀጠልም የባሌ ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ ውስጥ የተለያዩ እንስሳትንና አእዋፍን ተመለከቱ። ከዚያም ጅማ ተጉዘው የንጉስ አባጅፋርን ቤተመንግስት አዩ። በመጨረሻም ወደነቀምቴ ሄደው የንጉስ ኩምሳ ሞረዳን ቤተመንግስት የመጎብኘት እድል አገኙ።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ

### ተግባር አራት

**በመጀመሪያ ከዚህ በታች የቀረበውን ማስታወሻ አንብቡ፤ ከዚያም የተረዳችሁትን ሀሳብ አሳጥራችሁ ጻፉ፤ በመጨረሻም የጻፋችሁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተራ በተራ አንብቡላቸው።**

**ማስታወሻ**

**የአንቀጽ ባህርያት**

አንቀጽ ስለአንድ ሀሳብ ከሚገልጹ አረፍተነገሮች የሚዋቀር አነስተኛ የድርሰት ክፍል ነው። አንቀጽ ሶስት ባህርያት አሉት። እነሱም፡- አንድነት፣ ግጥምጥምነት እና ምሉዕነት ናቸው።

**አንድነት፡** የአንቀጽ አረፍተነገሮች በሙሉ የአንቀጹን ዋና ሀሳብ የሚደግፉ መሆን አለባቸው።

**ግጥምጥምነት፡** አረፍተነገሮች በቅደምተከተል ተገጣጥመው ወይም ተሰናስለው መፍሰስ (መጓዝ) አለባቸው፤

**ምሉዕነት፡** በአንቀጽ ውስጥ ጥያቄ የሚያስነሱ ሀሳቦች ካሉ በበቂ አረፍተነገሮች መብራራት አለበት።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት**

## ተግባር አምስት

**ስለእነቦንቱ ጉብኝት በ "ለ" ስር የቀረበውን አንቀጽ መሰረት አድርጋችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልሱ። ለመልሳችሁም ምክንያት ስጡ።**

1. አንቀጹ አንድነት አለው። ለምን?
2. አንቀጹ ግጥምጥምነት አለው። ለምን?
3. አንቀጹ ምሉዕነት አለው። ለምን?

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሶስት**

# ትምህርት አምስት፡ ቃላት

## መልመጃ ሶስት

**ሀ. ለሚከተሉትን ቃላት እና ሀረጋት ተመሳሳያቸውን ሰጥታችሁ ዓረፍተነገር መስርቱባቸው።**

ምሳሌ፡ አራዊት - የዱር እንስሳት

በባሌ ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ በርካታ **የዱር እንስሳት** አሉ።

1. ጉብኝት
2. ፓርክ
3. መልከዓ ምድር
5. ግጥምጥምነት
6. አንድነት
7. ምሉዕነት

4. የቱሪስት መስህቦች

8. አንቀጽ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት**

**ለ. ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒያቸውን ከሰጣችሁ በኋላ ዓረፍተነገር መስርቱባቸው።**

ምሳሌ፡ ተራራማ - ሜዳማ

የሀገራችን አብዛኞቹ ሜዳማ ስፍራዎች በደን አልተሸፈኑም።

1. ሙቀት
2. ከተማ
3. ቁልቁለት
4. የዱር እንስሳት
5. ሀዘንተኛ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት**

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

ከአማርኛ ቃል ክፍሎች አንዱ ቅጽል ነው። ቅጽል ከስም በፊት እየገባ የስሙን መጠን፣ መልክ እና ሁኔታ ይገልጻል።

ለምሳሌ፡ "ትልቅ ዛፍ" የተሰመረበት ቃል ቅጽል ነው፣ ምክንያቱም ዛፍ ላይ ተቀጥሎ የዛፉን ሁኔታ ይገልጻል።

## መልመጃ አራት

ሀ. በምሳሌው መሰረት ቅጽል ስምን ሲገልጽ የሚያሳዩ አምስት ሀረጋት መስርቱ።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት**

ለ. ከሚከተሉት ሀረጋት ቅጽል የሆኑትን በመለየት አመልክቱ።

1. ፈጣን መኪና
2. ሯጭ ፈረስ
3. ረጅም መንገድ
4. ሠካራም ሰው
5. ደማቅ አበባ
6. ብልህ ተማሪ
7. ጠመዝማዛ ወንዝ
8. ተወርዋሪ ኮከብ
9. ገደላማ ቦታ
10. ቡናማ ዐይን

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት**

ሐ. የሚከተሉትን ቅጽሎች በባዶው ስፍራ በመጠቀም ሀረጋት መስርቱ።

ጎበዝ፣ ሩቅ፣ ነጭ፣ ዳመናማ፣ ድፍርስ

1. ________ሀገር
2. ________ተማሪ
3. ________ቀን
4. ________ውሃ
5. ________መኪና

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት

መ. በሰንጠረዡ ውስጥ ለቀረቡት ቃላት በትይዩአቸው ቅጽል ነው ወይም ቅጽል አይደለም በማለት ጻፉ።

| ቃላት | መልስ |
|---|---|
| ሰነፍ | |
| ገለጻ | |
| ትልቅ | |
| የዋህ | |
| ጨከነ | |
| ደግ | |
| ረጅም | |

# ምዕራፍ ስድስት፡ ስፖርት

**ክፍለጊዜ፡ አንድ**

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

**በዚህ ትምህርት ክፍል የሚደመጥ ምንባብና የተለያዩ መልመጃዎች ቀርበዋል። የሚሰጡትን ትዕዛዛት እየተከተላችሁ ተግብሯቸው።**

### ቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ከአገራችን አትሌቶች እነማንን ታውቃላችሁ?
2. ከታዋቂ ሯጮች ማንን ይበልጥ ታደንቃላችሁ? ለምን?
3. ከዚህ በታች በፎቶ ከቀረቡት አትሌቶች መካከል የምታውቋቸውን ስማቸውን ተናገሩ።








## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. አምስት የቀድሞ አትሌቶችን ስም ዘርዝሩ፡፡
2. ከቀድሞ አትሌቶች በመቀጠል ታዋቂ የሆኑ አምስት አትሌቶችን ስም ጥቀሱ፡፡

**ክፍለጊዜ፡ ሁለት**

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

**ሀ. በተደመጠው ምንባብ መሠረት "እውነት" ወይም "ሐሰት" በማለት መልሱ።**

1. ከቀድሞዎቹ አትሌቶች አበበ ቢቂላና ማሞ ወልዴ ይጠቀሳሉ።
2. ኢትዮጵያ ስሟ ተደጋግሞ የሚነሳው በእግር ኳስ ውድድር መስክ ነው።
3. ኃይሌ ገብረስላሴ በአትሌቲክስ ሲሳተፍ የነበረው በውሱን ውድድሮች ብቻ ነው።
4. ደራርቱ ቱሉ የመጀመሪያውን የወርቅ ሜዳሊያ ያገኘችው በበርሊን ኦሎምፒክ ነበር።
5. ደራርቱ ቱሉ በአፍሪካ አትሌቲክስ ሻምፒዮና ክብረወሰን በመስበር የወርቅ ተሸላሚ ሆናለች።

**ለ. በ "ሀ" ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳያቸውን ከ "ለ" ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ**

| ሀ | | ለ | |
|---|---|---|---|
| 1. | አለምአቀፍ | ሀ. | የማሸነፍ ብስራት |
| 2. | ሜዳሊያ | ለ. | ዘዴ |
| 3. | ፍጻሜ | ሐ. | መጨረሻ |
| 4. | ድል | መ. | ሽልማት |
| 5. | ብልሃት | ሠ. | ብዙ አገሮች |
| | | ረ. | ውድቀት |

**ክፍለጊዜ፡ ሶስት**

**ሐ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ**

1. ከቀደሙት አትሌቶች አንዱ የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. ቀነኒሳ በቀለ ሐ. ፈይሣ ሌሊሳ

   ለ. ኃይሌ ገ/ስላሴ መ. አበበ ቢቂላ

2. አትሌት ደራርቱ ቱሉ መጀመሪያ ድል ያደረገችው የት ነው?

   ሀ. በቡልጋሪያ ኘሎቭዴቭ

   ለ. ስፔን ባርሴሎና

   ሐ. አውስትራሊያ ሲደኒ

መ. ጃፓን ቶክዮ

3. ኃይሌ ገብረ ስላሴ የኦሎምፒክ ባለድል የሆነው ስንት ጊዜ ነው?

ሀ. አራት ጊዜ　　ሐ. አንድ ጊዜ

ለ. ሁለት ጊዜ　　መ. ሶስት ጊዜ

4. ደራርቱ ቱሉ የመጀመሪያውን ኦሎምፒክ ድል ያገኘችው________

ሀ. በታዳጊ ወጣቶች ውድድር

ለ. በአዋቂዎች የሴቶች ውድድር

ሐ. በህጻናት ውድድር

መ. በጎልማሶች ውድድር

5. ኢትዮጵያ የታወቀችበት የአትሌቲክስ ውድድር

ሀ. ዝላይ　　ሐ. ውርወራ

ለ. ሩጫ　　መ. መልሱ የለም

6. አገራችን ኢትዮጵያ በአትሌቶታችን የምትኮራው ለምንድነው?

ሀ. በአሸናፊነታቸው

ለ. አገሪቱን ለዓለም በማስተዋወቃቸው

ሐ. ባንዲራችንን በማውለብለባቸው

መ. ሁሉም መልስ ነው

7. በተመሳሳይ ዘመን የነበሩት የትኞቹ ናቸው?

ሀ. ደራርቱ ቱሉ እና አበበ ቢቂላ

ለ. ኃይሌ ገብረ ስላሴ እና ማሞ ወልዴ

ሐ. ደራርቱ ቱሉ እና በላይነህ ዲንሳሞ

መ. ኃይሌ ገብረሥላሴ እና ደራርቱ ቱሉ

**ክፍለጊዜ፡ አራት**

**ሠ. ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ በመስጠት ባገኛችሁት መልስ አረፍተነገር ሥሩ።**

ምሳሌ፡- በላ፡ ተመገበ

**አረፍተነገር፡** ጫላ ምሳውን ተመገበ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ተጠቃሽ | ትኩረት | ገናና | ውድድር | ማጀብ |
| ውብ | ቀድሞ | ብቃት | ድንቅ | |

**ክፍለጊዜ፡ አምስት**

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### ተግባር አንድ

ታዋቂ ስለሆኑ ሁለት አትሌቶች (ለምሳሌ ቀነኒሳ በቀለና ገንዘቤ ዲባባ) የህይወት ታሪክ ወላጆቻችሁን ወይም ሌሎች ሰዎችን ጠይቃችሁ መረጃ አጠናቅሩ። የተገኘውን መረጃም ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ።

**ክፍለጊዜ፡ ስድስት**

## ተግባር ሁለት

በመጀመሪያ በእግር ኳስ ስፖርት ታዋቂ የሆኑ አንድ የቀድሞ እና አንድ የአሁን ዘመን ተጫዋቾች ምረጡ። በመቀጠል ስለተጫዋቾቹ ሰዎችን ጠይቃችሁ መረጃ አሰባስቡ። ከዚያም ያሰባሰባችሁትን መረጃ ክፍል ውስጥ በሚደረግ ውይይት አዳብሩ፡፡ በመጨረሻም በቃል ለክፍል ተማሪዎች በተወካያችሁ አማካኝነት አቅርቡ።

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**

# ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

## ምንባብ አንድ

**የሚከተለውን ምንባብ ጥንድ ጥንድ በመሆን አንቀፆቹን ተከፋፍላችሁ ተራ በተራ ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ አንብቡ።**

## ሴት አያቴ

ሴት አያቴ ሁልጊዜ ማታ ማታ ተረት ትነግረኛለች። የምትነግረኝ ተረት ብዛትና አይነት ዛሬም ድረስ ይገርመኛል። ከተረቶቿ መካከል ስለጦጣና አንበሳ፣ ስለዔሊና ጥንቸል፣

ስለአይጥና ድመት፣ ስለሞኙ ልዑል የነገረችኝ ፈፅሞ አይረሳኝም። አያቴ በተረቶቹ አማካኝነት እያዝናናች አስተምራኛለች፤ እኔ ጥሩ ባህሪ ያለኝ ሰው እንድሆን ብዙ ለፍታለች። እኔም እንደማላሳፍራት ቃል ገብቻለሁ።

አያቴ እንደምትለው ለኔ የምትነግራቸውን ተረቶች በሙሉ ያገኘችው እሷም እንደኔ ከአያቷ ነበር። አያቴ ማታ ማታ የምትነግረኝን ተረቶች እኔ ደግሞ እረኛ ለሆኑ ጓደኞቼ ቀን ቀን እተርክላቸው ነበር። ለዚህም ሁል ጊዜ በጉጉት ይጠብቁኛል። የአያቴ ተረቶች ደግ፣ ለሰዎች አሳቢ፣ ጥሩ ተፎካካሪ፣ ችግርን የምንቋቋም እንድንሆን አግዘውናል።

**ክፍለጊዜ፡ ስምንት**

## የቅድመማንበብ ጥያቄዎች

**የሚከተሉት ጥያቄዎችን በቃል መልሱ።**

1. በአካባቢያችሁ የሚዘወተሩ የአካላዊ እንቅስቃሴ ምን ምን ናቸው?
2. አካላዊ እንቅስቃሴ ማድረግ ለምን ይጠቅም ይመስላችኋል?
3. የተከታዮቹን ቃላት ፍች ገምቱ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| አካል ብቃት፣ | ምርታማ፣ | እንዲወገዱ፣ | የሰለጠኑ |

# የአካል ብቃት እንቅስቃሴ

ከስፖርት አይነቶች አንዱ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ (ጂምናስቲክ) ነው። የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ከሰው ልጅ የዕለት ተዕለት ተግባሮች ጋር የተያያዘ ነው። ሰዎች ለሚያከናቸው ተግባራት ጡንቻዎቻቸውን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ይጠቀማሉ። አካላዊ እንቅስቃሴ ደግሞ እነዚህን ጡንቻዎች ጠንካራና ጤናማ እንዲሆኑ ያግዛል። የእጅና የእግር ጡንቻዎች ጠንካራና ጤናማ ከሆኑ ብዙ ስራዎች እንዲሰሩና ምርታማነት እንዲጨምር ያስችላሉ።



አካላዊ እንቅስቃሴ ጡንቻዎችን ብቻ ሳይሆን ሌሎች ውስጣዊ የአካል ክፍሎቻችንም በአግባቡ ስራቸውን እዲሰሩ ያስችላቸዋል። የተሳለጠ የደም ዝውውርም በደምስሮች ውስጥ እንዲኖር ሁኔታዎችን ያመቻቻል። ከዚህም ሌላ አለአግባብ በሰውነታችን ውስጥ የሚከማች ስብን በማቃጠልና ቆሻሻዎች


ከሰውነታችን ውስጥ እንዲወገዱ በማድረግም የበኩሉን ሚና ይወጣል።

1. ከሰው ልጅ የእለት ተእለት ህይወት ጋር የተያያዘው ተግባር ምንድን ነው?
2. የአካል ብቃት እንቅስቀሳሴ ምን ጥቅም አለው?
3. የአካል ብቃት እንቅስቃሴ በምን መልኩ የሚመራ ይመስላችኋል?



አካላዊ እንቅስቃሴን በተመለከተ ሊታወቅ የሚገባው ነገርም አለ። ይኸውም ተግባሩ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ መመራት ያለበት መሆኑ ነው። አንድ አካላዊ እንቅስቃሴ ለመስራት የሚነሳ ሰው ምን፣ መቼ፣ እንዴትና በምን አይነት መሳሪያዎች ወይም ሁኔታዎች ታግዞ እንደሆነ አስቀድሞ ማወቅ አለበት። ለአለባበስም ቢሆን ትኩረት ሊሰጥ ይገባል። ለዚህም መፅሀፍትን ማንበብና የሰለጠኑ የስፖርት ባለሞያዎችን ማማከር ይገባል።

የተዘጋጁ የመማሪያ ቪዲዮዎችም በአማራጭነት ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ። ያለበለዚያ ግን የሰውነት አካላት ያልተጠበቀ ጉዳት ሊያስተናግዱ ይችላሉ።



**ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ**

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

**ሀ. የሚለተሉትን አረፍተነገሮች በምንባቡ መሰረት “እውነት” ወይም “ሐሰት” እያላችሁ መልሱ።**

1. አካላዊ እንቅስቃሴን ተወዳዳሪ የሆኑ ስፖርተኞች ብቻ ሊያከናውኑት ይገባል።
2. አካላዊ እንቅስቃሴ ጡንቻዎች ጠንካራና ጤናማ እንዲሆኑ ያግዛል።
3. አካላዊ እንቅስቃሴ የደም ዝውውር እንዲደናቀፍ ሁኔታዎችን ያመቻቻል።

4. አካላዊ እንቅስቃሴ ቆሻሻን ያስወገዳል፤ የተከማቸ ስብን ያቀልጣል።
5. የአካላዊ እንቅስቃሴ ተግባር ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ መመራት አለበት።

**ለ· ተከታዮቹን ጥያቄዎች አንብባችሁ ተገቢ መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ።**

1· የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ከሰው ልጅ_______ተግባሮች ጋር የተያያዘ ነው።

ሀ. የዕለት ተዕለት　　　ሐ. ጊዜያዊ

ለ. የድሮ　　　መ. የአመት አመት

2· የ ______________ ጡንቻዎች ጠንካራና ጤናማ ከሆኑ ብዙ ስራዎች እንዲሰሩና ምርታማነት እንዲጨምር ያስችላሉ።

ሀ. የደም ዝውውር　　　ሐ. እጅና የእግር

ለ. የጀርባ ላይ　　　መ. የሰለጠኑ ባለሙያዎች

3· አካላዊ እንቅስቃሴ ጡንቻዎችን ብቻ ሳይሆን ሌሎች ውስጣዊ ____________ በአግባቡ ስራቸውን እንዲሰሩ ያስችላቸዋል።

ሀ. የአካል ክፍሎቻችን　　　ሐ. የደም ዝውውር

ለ. አሰራሮችን　　　መ. ስብና ስብ ነክ

4· የተሳለጠ የደም ዝውውር የሚኖረው በ________ ውስጥ ነው።

ሀ. በሳንባ　　ሐ. በሰረሰሮች

ለ. በደምስሮች　　መ. እጅና እግር

5· አንድ አካላዊ እንቅስቃሴ ለመስራት የሚነሳ ሰው በቅድሚያ ማድረግ ያለበት ________

ሀ. ምን እንደሚሰራ　　ሐ. እንዴት እንደሚሰራ

ለ. መቼ እንደሚሰራ　　መ. ሁሉም መልስ ይሆናሉ

**ክፍለጊዜ፡ አስር**

ሐ· በ“ሀ” ስር ያሉት ሀረጎች የያዙትን ፍች ምንባቡ ውስጥ ያሉበትን አውድ በማየት በ“ለ” ስር ካሉት ጋር አዛምዱ።

| “ሀ” | “ለ” |
|---|---|
| 1. አካል ብቃት እንቅስቃሴ | ሀ. አስተማማኝ |
| 2. በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ | ለ. የድርሻውን |
| 3. ጠንካራና ጤናማ | ሐ. በሁሉም መንገድ |
| 4. የበኩሉን ሚና | መ. ድንገተኛ አደጋ |
| 5. ያልተጠበቀ ጉዳት | ሠ. ሰውነት ማጎልመሻ |

ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ

**መ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ከተወያያችሁ በኋላ በቃል መልሱ።**

1. አካል ብቃት እንቅስቃሴ ማድረግ የሚያስገኘውን ጠቀሜታ አስረዱ።
2. አንድ የአካል እንቅስቃሴ የሚያደርግ ሰው አስቀድሞ ምን ምን ነገሮችን ማሟላት እንደሚገባው ተናገሩ።
3. አካል ብቃት እንቅስቃሴ የሚያደርግና አካል ብቃት እንቀስቃሴ የማያደርግ ሰው መካከል የሚኖር ልዩነትን አብራሩ።
4. ምንባቡ ውስጥ ያሉትን አንቀፆች ወደኋላ ተመልሳችሁ አንብቧቸውና ዋና ጭብጣቸው ምን እንደሆነ (ስለምን እንደሚነግሩን) አስረዱ።

ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት

# ትምህርት አራት፡ ቃላት

## መልመጃ ሶስት

**ሀ. በተከታዮቹ አረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍቺ የሚሆኑትን በመምረጥ መልሱ።**

1· ስፖርታዊ <u>**ውድድሮች**</u> ተፎካካሪነትን በማሳደግ ብዙዎች እንዲሳተፉባቸው ያደርጋሉ።

ሀ. ሽንፈቶች　　　ሐ. ድራማዎች

ለ. ጨዋታዎች　　　መ. ትጥቆች

2· ሉሲ የሴቶች እግር ኳስ ቡድን ተቀናቃኟን ስምንት <u>**ለምንም**</u> ረታች።

ሀ. ለስምንት　ለ. ለሁለት　ሐ. ለአንድ　መ. ለዜሮ

3· በተራ ቁጥር 2 ስር '**ረታች**' የሚለውን ቃል ሊተካ የሚችለው የትኛው ነው?

ሀ. ተሸነፈ　ለ. አሸነፈች　ሐ. መታች　መ. ወጣች

4· በመረብ ኳስ ጨዋታ ሁለት <u>**ተቀናቃኝ**</u> ቡድኖች ተሳታፊ ይሆናሉ።

ሀ. ተፎካካሪ　ለ. አሸናፊ　ሐ. ጠላት　መ. ተሸናፊ

5· በተራ ቁጥር 4 ስር '**ተሳታፊ**' የሚለውን ቃል ሊተካ የሚችለው የትኛው ነው?

ሀ. አገልጋይ　ለ. ተካፋይ　ሐ. ወዳጅ　መ. ዳኛ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሦስት**

**ለ· የሚከተሉትን ቃላት ፍች ከሰጣችኋቸው በኋላ አረፍተነገር መስርቱባቸው።**

| | | |
|---|---|---|
| ድል | አሸናፊ | ነጥብ |
| በረኛ | ደጋፊ | ተሸናፊ |

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት**

# ትምህርት አምስት፡ መጻፍ

## መልመጃ አራት

**ሀ. ተከታዮቹን ቃላት ወይም ሀረጋት በመጠቀም የየራሳችሁን አረፍተ ነገሮች መስርቱ።**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ስፖርት | አካላዊ እንቅስቃሴ | ዋንጫ | እግር ኳስ |
| ጤናማ | ተወዳዳሪ | በራስ መተማመን | ጥንካሬ |

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት**

**ለ. የሚከተሉትን ያልተስተካከሉ አረፍተነገሮች እንደገና አስተካክላችሁ ፃፉ።**

**ምሳሌ፡** እነሱ ዛሬ ወደኳስ ሜዳ ሄደ።

እነሱ ዛሬ ወደ ኳስ ሜዳ ሄዱ።

1. እኔና አንቺ ጥናታችሁን እናጥና።
2. ደራርቱ በፍጥነት ወደ ቤቷ ሂደ።
3. አጎቴ መጣች።

4· ሰውዬው ብርጭቆውን ተሰበረ።

5· እኔ አገሬን ትወዳለች።

6· ልጆቹ ኳስ ተጫወቱ ነው።

7· ሁለት አትሌቶች ዛሬ ይመጣል።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት

**የሚከተሉትን በምሳሌው መሰርት ስሩ።**

**ምሳሌ፡** መሬማ ወደትምህርት ቤት _________።

መሬማ ወደትምህርት ቤት ሄደች።

1· ልጆቹ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ _______ ነው።

2· ትምህርት ቤት ከመሄዴ በፊት ቁርሴን ______።

3· አቶ ኅበና ተወዳጅ መምህር _________።

4· ወይዘሮ ብርሃኔ የታመመ ለ_________ ሄዱ።

5· ዜጎቿ ጠንክረው ከሰሩ ሀገራችን ከድህነት _____።

6· ትምህርት ቤት ደርሰን የህዝብ መዝሙር _____።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት

**በተከታዮቹ አረፍተነገሮች ውስጥ ያሉ ስህተቶች በምን የተነሳ እንደተፈጠሩ አስረዱ። አረፍተነገሮቹንም አስተካክላችሁ ፃፉ።**

ምሳሌ፡ እሳቸው ዛሬ በጊዜ መጣች። (ባለቤትና ማሰሪያ አንቀፅ አለመስማማት)

**ሲስተካከል፡ እሳቸው ዛሬ በጊዜ መጡ።**

1. እህቴ ደብዳቤ ፃፈ ለኔ።
2. አበበ ስልክ ተደወለልኝ።
3. የተሰጡት ክፍለጊዜዎች አለቀ።
4. ለሊሴና አሰለፈች እህትማማቾች ነው።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

**በ 'ሀ' ስር ለቀረቡት በ'ለ' ስር ካሉት የሚስማማቸውን እየመረጣችሁ አዛምዱ።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. የተተከሉ ዛፎችን | ሀ. ኤሌክትሪክ አመነጨ። |
| 2. የስደት ኑሮ ሲያስመርረው | ለ. ውሃ እናጠጣቸው። |
| 3. ልጆች መንገድ ላይ | ሐ. እየተለመደ ነው። |
| 4. ታላቁ የህዳሴ ግድብ… | መ. ሊጠበቁ ይገባል። |
| 5. ህፃናት ከአደጋ… | ሠ. ወደ ሀገሩ ገባ። |
| 6. ዘመናዊ አኗኗር | ረ. ሃዲድ ተገነባ። |
| | ሰ. አይጫወቱ። |

# ምዕራፍ ሰባት፡ ውሃ

ክፍለጊዜ፡ አንድ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

በዚህ ትምህርት ክፍል ‘የውሃ ጥቅም’ የተሰኘ ምንባብ እንድታዳምጡ ቀርቦላችኋል። ምንባቡን ተከትሎም የተለያዩ ተግባራትና መልመጃዎች ቀርበውላችኋል። ትዕዛዛቱን እየተከተላችሁ ስሯቸው።

### የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

1. በአከባቢያችሁ ያሉ ማህበረሰቦች ውሃ የሚያገኙት ከየት ነው?
2. በአከባቢያችሁ ውሃ ለምን ለምን ጥቅሞች ይውላል?
3. የሚከተሉትን ቃላት ፍች ገምቱ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| አገልግሎት፣ | ፍጆታ፣ | ቱሪዝም፣ | ማዘውተር፣ | ጎብኚ |

### የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

እነዚህን ጥያቄዎች መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ እያዳመጣችሁ መልሱ።

1. በገጠርና በከተማ አካባቢዎች ውሃ ለምን አገልግሎት ይውላል?

2. የውሃ ሌላው አገልግሎቱ ለ________ስራ መዋሉ ነው።

3. በአጭር ጊዜ ምርት የሚሰጡ የተባሉት እነማን ናቸው?

**ክፍለጊዜ፡ ሁለት**

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

**ሀ. ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት የሚከተሉትን "እውነት" ወይም "ሐሰት" በማለት መልሱ።**

1. የሕዝብ ቁጥር ሲጨምር የውሃ ፍላጎት ግን ይቀንሳል።
2. ውሃ በቤት ውስጥ እና ውጪ በሚሰጠው ጥቅም ይወሰናል።
3. ውሃን ገድቦ በመስኖ መጠቀም ምርት እንዲቀንስ ያደርጋል።
4. ውሃ ባይኖርም ለተለያዩ ፍጆታዎች የሚውሉ ምርቶች ይመረታሉ።
5. ውሃ በቱሪዝም ሀብትነት የሚሰጠው ጥቅም ከፍተኛ ነው።

**ለ. ባዳመጣችሁት መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. የሕዝብ ቁጥር ሲጨምር ውሃ ለምን ያንሳል?
2. በምንባቡ መሰረት የውሃ ጥቅሞች የተባሉት እነማን

ናቸው?

3. ውሃ ለቱሪዝም እንዴት ያገለግላል?

4. በኢትዮጵያ መስኖ መጠቀም ምን ችግር ይፈታል?

5. በንፅህና ረገድ የውሃ ጥቅም ምን ምን ነው?

**ክፍለጊዜ፡ ሦስት**

**ሐ. የሚከተሉት ቃላት ምንባቡ ውስጥ የያዙትን ፍች በማየት ካዛመዳችሁ በኋላ አረፍተነገር መስርቱ።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ማዘውተር | ሀ. ይጎበኛሉ |
| 2. ያስሳሉ | ለ. አገልግሎት ላይ የሚውል |
| 3. ፍጆታ | ሐ. መደጋገም |
| 4. አገልግሎት | መ. ጥቅም |
| 5. ምድራችን | ሠ. አለማችን |
| | ረ. ጨዋታዎች |

**ክፍለጊዜ፡ አራት**

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### ተግባር አንድ

በአከባቢያችሁ ውሃ የሚሰጣቸውን ጥቅሞች በተመለከተ፣ ሰዎች በአግባቡ እየተጠቀሙት ስለመሆን አለመሆኑና ወደፊት

ከመበከል ስጋት ነፃ እንዲሆን ምን ማድረግ እንደሚገባ መረጃ አጠናቅሩና በክፍል ውስጥ ተወያዩበት።

**ክፍለጊዜ፡ አምስት**

**ሀ. የሚከተሉትን ስዕሎች እዩና ውሃን በተመለከተ ምን ምን ተግባራት እንደተከናወኑ ፃፉና ለጓደኞቻችሁ በቃል አስረዱ።**



**ክፍለጊዜ፡ ስድስት**

**ለ. በሁለት ቡድን ተከፈሉና 'ቆሻሻ ውሃን መልሶ መጠቀም ይገባል አይገባም' በሚለው ነጥብ ላይ ክርክር አካሂዱ።**

(በክርክሩ ወቅት ተሳታፊዎች፣ ፀሐፊ፣ ነጥብ ያዥና ዳኞች ይኖራሉ)

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**


ሐ. ከዚህ በታች ያለውን የመዝሙር ግጥም ከመምህራችሁ ጋር በመሆን አጥኑና ክፍል ውስጥ በህብረት ዘምሩ።

## ውሃ

ውሃ ሕይወታችን
ለጥም እርካታችን
እድፍ ለማስወገድ ለንፅህናችን
ምግብ አበሳስሎ አጣፍጦ ለመብላት
ለሰውነት ቁጥጥር ለመጠበቅ ሙቀት
ዋና መሠረቱ ለሕልውናችን
መሆኑን እወቁ ለኛ አስፈላጊያችን(2ጊዜ)
ውሃ ለግብርናው
ለሐይል ማመንጫው
ለልማቱ ሁሉ ቁልፍ ጠቃሚ ነው (2ጊዜ)
የውሃ መገኛዎች
ወንዝና ሐይቆች
ድርቅ እንዳይጎዳቸው
ደኖችን በመትከል እንታደጋቸው (2ጊዜ)

**ክፍለጊዜ፡ ስምንት**

# ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ




## ቅድመማንበብ ጥያቄዎች

1. ውሃ ጥቅሙ ምንድን ነው?
2. ውሃ ከየት ይገኛል?
3. ውሃ ባይኖር ምን እንሆን ነበር?

## ውሃ

ሕይወት ላላቸው ነገሮች በሙሉ ውሃ አስፈላጊ ነው። ሰዎች፣ እንስሳትና ዕፅዋት ያለ ውሃ መኖር አይችሉም። ሰዎች ውሃን ለመጠጥ፣ የግል ንፅህናን ለመጠበቅ፣ ምግብ ለማብሰል እና ልብስና ቁሳቁስን ለማጠቢያነት ይገለገሉበታል። ከዚህም በተጨማሪ ውሃ ለኃይል ምንጭነት፣ ለመስኖ፣ ለደን ልማት፣

ለእርሻ ሰብል እና ለመሳሰሉት ተግባራት ማካሄጃነት ጥቅም ላይ ይውላል።

1. ሰዎች ውሃን ለምን ለምን አገልግሎት ይጠቀማሉ?

ውሃ በሰውነታችን ውስጥም በርካታ ተግባራትን ያከናውናል። ምግብና ማዕድናት በደም ውስጥ የሚዘዋወሩት በውሃ አማካይነት ነው። የተለያዩ ቆሻሻዎችም ከሰውነታችን ውስጥ በውሃ አማካይነት ይወገዳሉ። የሰውነት ፈሳሽ ሚዛን የሚጠበቀው በውሃ ነው። ውሃ የሰውነትን ሙቀት በመቆጣጠር ረገድም ወሳኝ ሚና ይጫወታል። ከተለያዩ ንጥረምግቦች እጥረት ይልቅ የውሃ እጥረት በሕይወት የመቆየትን ጥያቄ አደጋ ውስጥ ያስገባል። ያለ ውሃ ከቀናት በላይ በሕይወት መቆየት እንደማይቻል የተለያዩ የምርምር ውጤቶች ያረጋግጣሉ።

2. ውሃ በሰውነታችን ውስጥ የሚሰጠው ተግባራት ምን ምን ናቸው?

ውሃ ለመጠጥ ከመዋሉ ባሻገር ለኃይል ምንጭነትም ሊያገለግል ይችላል። በዚህም ወንዞች ተገድበው ለኤሌክትሪክ ኃይል ምንጭነት ያገለግላሉ። ለምሳሌ ሀገራችንም የግልገል ጊቤ፣ የተከዜ፣ የአዋሽ፣ የቆቃና የአባይ ወንዝ ግድቦች ዋነኞቹ ናቸው።

በአጠቃላይ የተጠቀሱትንና ሌሎች መሰል የውሃ ጥቅሞችን ለማስቀጠል ውሃን በአግባቡ መጠቀም ይገባል። ለዚህም ከተለያዩ በካይ ነገሮች መጠበቅ፣ ፍሰቱ እንዳይስተጓጎል ደንን በብዛትና ጥራት መትከል፣ የውሃ ብክነትን ከሚያስከትሉ ተግባራት መራቅ የሚስፈልግ ይሆናል።

**ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ**

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሶስት

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት "እውነት" ወይም "ሐሰት" በማለት መልሱ።**

1. ምግብና ማዕድናት በደም ውስጥ የሚዘዋወሩት በውሃ አማካይነት ነው።
2. ያለ ውሃ ከቀናት በላይ በሕይወት መቆየት እንደሚቻል ተረጋግጧል።
3. ወንዞች ተገድበው ለኤሌክትሪክ ኃይል ምንጭነት ያገለግላሉ።
4. የውሃ ጥቅሞችን ለማስቀጠል ውሃን በአግባቡ መጠቀም ይገባል።
5. ውሃን ሳይባክን ለመጠቀም የደን ምንጣሮ ዋነኛው መፍትሄ ነው።

## ክፍለጊዜ፡ አስር

**ለ. በ 'ሀ' ስር ከተሰጡት ሀሳቦች ግንኙነት ያላቸውን ከ'ለ' ስር እየመረጣችሁ አዛምዱ።**

ሀ

1. ለተወሰኑ ቀናት ውሃ ባይጠጣ…
2. ውሃን በመጠቀም ኤሌክትሪክ መመንጨቱ…
3. በውሃ አማካኝነት ንፅህናችንን መጠበቃችን…
4. ደኖች በጥራትና በብዛት መተከላቸው…
5. የእርከንና ግድቦች ስራ በብዛት መሰራቱ…

ለ

ሀ. … ለሰው ልጆች የሀይል አቅርቦት አስገኝቷል።

ለ. … የዝናብ መጠኑ እንዲጨምር ያደርጋሉ።

ሐ. …ከተለያዩ በሽታዎች እንድንጠበቅ አስችሏል።

መ. …የአፈር መሸርሸርን በእጅጉ ቀንሶታል።

ሠ. …በህይወት ይቆያል ተብሎ አይታሰብም።

**ሐ. ተስማሚ መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ።**

1. የወንዝ ውሃ ለሰዎች ፍጆታና ለ ___________ ማመንጫነት ያገለግላል።

   ሀ. መጠጥ　　　　ሐ. መስኖ

   ለ. ኤሌክትሪክ　　　　መ. ንፅህና

2. _____ ንፅህና ይጠበቅበታል ምግብ ይዘጋጅበታል

   ሀ. ሳሙና    ለ. ዘይት    ሐ. ውሃ    መ. ድስት

3. ከሚከተሉት አንዱ የውሃ ጥቅም ሊሆን አይችልም፤ የቱ ነው?

   ሀ. ለመስኖ    ሐ. ለኃይል ማመንጫነት

   ለ. ለመጠጥነት    መ. መልሱ አልተሰጠም

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ**

# ትምህርት አራት፡ መፃፍ

## መልመጃ አራት

**ሀ. የተዘበራረቁትን ቃላት በማስተካከል የተሟላ ዓረፍተነገር መስርቱ።**

1. ጠንቅ ውሃ ለጤና የተበከለ ።
2. አፍልተንና ውሃ አቀዝቅዘን አለብን የወንዝን መጠጣት ።
3. መጠጣት ውሃን የምንጭ አጣርተን አለብን ።
4. ነው ወንዝ ጉደር   ወንዝ ገባር የአባይ።
5. አገልግሎት ይውላል ወንዝ ለመጓጓዣ የባሮ።
6. ወረዳ የአዋሽ ወንዝ መነሻ ደንዲ ነው።
7. በበርካታ የሚጎበኝ ወንጪ ውብ ነው ቱሪስቶች ስፍራ ሀይቅ።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት

**ለ. የሚከተሉትን ያልተሟሉ ዓረፍተነገሮች ቀጥሎ ባሉት ሀረጋት አሟልታችሁ ጻፉ።**

| | | |
|---|---|---|
| አስፈላጊ ነው | በክረምት ነው | እንዲጨምር ይረዳል |
| ማመንጨት ይቻላል | ህይወት ነው | በክረምት ወቅት |
| ይሞላሉ | | |

ምሳሌ፡ ውሃ ለሰውነታችን ____________

ውሃ ለሰውነታችን <u>አስፈላጊ ነው።</u>

1. በበጋ ወቅት መስኖ ውሃ መጠቀም የግብርና ምርት________።
2. ውሃ በመገደብ የኤሌክትሪክ ኃይል____________።
3. የዝናብ ውሃ በአብዛኛው የሚገኘው____________።
4. ውሃ ________።
5. አብዛኞዎቹ የሀገራችን ግድቦች____________።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሶስት

**ሐ. የሚከተሉትን ቃላት በመጠቀም የተሟሉ ዓረፍተነገሮች ጽፋችሁ ለጓደኞቻችሁ ተራ በተራ አንብቡ።**

| | | |
|---|---|---|
| ማዕድን | ሚና | እጥረት |
| መቆጣጠር | ሰውነት | ሰብል |
| ፈሳሽ | ኃይል | ልማት |
| ግድብ | ሐዳሴ | ፍጆታ |

ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት

# ትምህርት አምስት፡ ቃላት

## መልመጃ አምስት

ሀ. ከሚከተሉት ቃላት ተስማሚውን በመምረጥ በባዶ ቦታው አሟሉ።

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ዳቦ | ገጠመ | ተጫወተ | ቆሎ | አገዳ | ከብት |
| ላሚቷን | መሬቱን | መንገድ | አጨዳ | አጠበ | |

1. ፋጡማ __________ አለበች።
2. ግርማ የተሰጠውን __________እየገመጠ በላ።
3. ሌሊሴ ግራ ቀኟን በማየት_________አቋረጠች።
4. ናታን የተሰጠውን ________ ቆረጠመ።
5. በላቸው ከጠዋት ጀምሮ በበሬዎቹ ______አረሰ።
6. የ _______እርባታ አንዱ የእርሻ ክፍል ነው።
7. ጉደታ ልብሱን በውሃ እና በሳሙና ______።
8. ኃይሉ የሠራውን በር በቤቱ ________።

ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

## መልመጃ ስድስት

ሀ. ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች በትይዩአቸው ከቀረቡት ተስማሚውን ግስ በመምረጥ ዓረፍተነገር መሥርቱ።

ምሳሌ፡ እኛ ውሃ______። / ጠጣ፣ ጠጣን፣ ጠጣሁ/

እኛ ውሃ ጠጣን።

1. ገመቹ ወደ ትምህርት ቤት____።/ሄድን፣ ሄዱ፣ ሄደ/
2. እነ በሬዱ ኳስ____።/ተጫወተች፣ተጫወተ፣ ተጫወቱ/
3. እነሱ ትላንትና ምግብ ______ ።/ በላ፣ ይበላሉ፣ በልተዋል/
4. ገረመው ነገ ፈተና ____። /ተፈተነ፣ ይፈተናል፣ ተፈትኗል/
5. እኔ የአራተኛ ክፍል ተማሪ __ ።/ ነኝ፣ ነህ፣ ነን/

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት**

ለ. በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተነገር መስርታችሁ ለክፍል ተማሪዎች አንብቡ።

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አፀዳ፣ | ቆየ፣ | ተከለ፣ | ፈቀደ፣ | ደረበ፣ | ጀመረ፣ | ጨረሰ |

## ክፍለጊዜ አስራ ሰባት

ሐ. ተስማሚውን ግስ በመምረጥ ዓረፍተነገሩን አሟሉ፡

| ወረደ፣ | ቆረጠ፣ | ቀጠፈ፣ | ወጣ፣ | ለበሰ |
|---|---|---|---|---|

1. አበበ ፈተናውን ለማለፍ በርትቶ ለማጥናት________፡፡
2. ገዳ አበባውን _______፡፡
3. ማቴዎስ ከቤቱ ጣራ ላይ በመሠላል______፡፡
4. ገምቴሳ የቢሮውን በር ዘግቶ ______፡፡
5. ገላና ከመኝታው ተነስቶ ልብሱን ______፡፡

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት

መ. ከሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ የግስ ገላጭ የሆነውን ቃል ከስሩ በማስመር ለዩ፡፡

ምሳሌ፡ ጌታቸው <u>በቀስታ</u> ተራመደ

1. ልጁ ከፉኛ ወደቀ፡፡
2. አንበሳው በፍጥነት ሮጠ፡፡
3. ተማሪዎች ገና አልመጡም፡፡
4. ጋሻው ምግቡን ቶሎ ቶሎ በላ፡፡
5. ተማሪው እያዘገመ መጣ፡፡

# ምዕራፍ ስምንት፡ ድርድር

## ክፍለጊዜ፡ አንድ

# ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

**በዚህ ትምህርት ክፍል የማዳመጥ ክሂላችሁን እንድታሻሽሉ የሚያግዙ መልመጃዎች እና ተግባራት ስለቀረቡ በትእዛዛቸው መሰረት በትኩረት ስሩ።**



## የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ምስሉን ተመልክታችሁ በቀጣይ ስለምን እንደምታዳምጡ ገምቱ።
2. በአካባቢያችሁ የሚገኙ ሰዎች ቅራኔያቸውን ለመፍታት ስለምን ጉዳዮች ሊደራደሩ ይችላሉ?
3. እናንተስ ከማን ጋር ስለምን ተደራድራችኋል?

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ተደራዳሪዎቹ ------- እና ------ ናቸው።
2. "ወሬህ ሁሉ ፍሬ ቢስ ነው" የተባለው -----ነው።
3. "አፍ አለኝ ብለህ ትናገራለህ" ያለው ------ ነው።
4. ተደራዳሪዎቹን ያስማማቸው ------- ነው።

**ክፍለጊዜ፡ ሁለት**

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

**ሀ. በአዳመጣችሁት መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች "እውነት" ወይም "ሀሰት" በማለት በቃል መልሱ።**

1. ሀሳቡን መጀመሪያ የጀመረው በጋ ነው።
2. ጭፍንፍን ጨለማ ብሎ የተሳደበው በጋ ነው።
3. የከሲታ ከብት ባለበት የተባለው በጋ ነው።
4. ንትርኩን እያረገበ የመጣው ክረምት ነው።
5. "ተቃራኒ ስንሆን ተደጋጋፊ ነን" ያለው ክረምት ነው።
6. "ስለጥቅማችን ሰዎችን እንጠይቅ" ያለው በጋ ነው።
7. "ጥላ በማስያዝ ትታወቃለህ" የተባለው ክረምት ነው።

**ክፍለጊዜ፡ ሶስት**

**ለ. በ "ሀ" ስር ያሉትን ቃላትና ሀረጋት በ"ለ" ከሚገኙት ፍች ዎቻቸው ጋር አዛምዱ።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. የዝናብ ወቅት | ሀ. በጋ |
| 2. በማደግ ላይ ያለእህል | ለ. ምርት |
| 3. ጥላ | ሐ. ዝናብ መከለከያ |
| 4. የሥራየመጨረሻ ውጤት | መ. ክረምት |
| 5. የጸሀይ ወቅት | ሠ. ቡቃያ |

**ክፍለጊዜ፡ አራት**

**ሐ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ**

1. በጋ ክረምትን ለምን ጭፍንፍን ጨለማ አለው?
2. ክረምት ደግሞ አንተ የከሲታ ከብቶች ባለቤት፣ ውሃ ጥማም ለምን አለው?
3. "ተሳስቻለሁ" ብሎ ያመነው ማነው?
4. "ሰዎች የሚደሰቱት በኔ ነው" ያለው ማነው? ለምን?
5. ከክረምት እና ከበጋ የቱ ይሻላል? ለምን?

**ክፍለጊዜ፡ አምስት**

**መ. ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳያቸውን ፈልጉላቸው፡**

ከንቱ ስስታም

| | |
|---|---|
| ልምላሜ | ቡቃያ |
| ጭፍን | ጉራ |
| ጨለማ | ተቃራኒ |

**ክፍለጊዜ፡ ስድስት**

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

**በዚህ ትምህርት ክፍል እንድትናገሩ የሚያደርጉ ተግባራት ስለቀረቡ በትእዛዛቸው መሰረት ስሩ።**

### ተግባር አንድ

ሀ. ጥንድ ሆናችሁ አንዳችሁ ሻጭ አንዳችሁ ገዢ ሆናችሁ ለመደራደር ተለማመዱ፤ ከዚያም ለክፍሉ ተማሪዎች አቅርቡ።

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**

ለ. ጥንድ ሆናችሁ ትምህርት የማይወድ እና ትምህርት የሚወድ ተማሪ መካከል ድርድር በመፍጠር አንደኛው ሌላኛውን ልጅ እንዲያሳምነው አድርጋችሁ ተለማመዱ፤ በመጨረሻም ድርድሩን ለክፍሉ ተማሪዎች አቅርቡ።

**ክፍለጊዜ፡ ስምንት**

## ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

### የባልና ሚስት ድርድር

## ቅድመማንበብ ጥያቄዎች

1. ባልና ሚስት ስለምን ሊደራደሩ ይችላሉ?
2. በባልና ሚስት ኑሮ ወሳኙ ማን ይመስላችኋል?

በወይዘሮ አለሚቱና በአቶ ጎሳ መካከል ለብዙ አመታት ታፍኖ የቆየ ብሶት ዛሬ በወይዘሮ አለሚቱ አነሳሽነት በጉዳዩ እንደሚከተለው ተነጋገሩበት።

**ወይዘሮ አለሚቱ፡** ጎሳ አንተና እኔ ከተገናኘን ጀምሮ በኑሯችን የኔ ሀሳብ ከአንተ ሀሳብ ጋር ብዙም ተዋህዶ አያውቅም፤ እስቲ ለዚህ ጉዳይ ፍቃድህ ከሆነ ብንነጋገር።

**አቶ ጎሣ፡** የምን ንግግር?

**ወይዘሮ አለሚቱ፡** ስለኑሯችን ነዋ፡፡

**አቶ ጎሳ፡** ምነው ዝም ብለሽ ኑሮሽን ብትኖሪ!

**ወይዘሮ አለሚቱ፡** ተው እንዲህ አትበል! ብንመካከር መልካም ነው።

**አቶ ጎሣ፡** የበላይ መሆን አማረሽ?

**ወይዘሮ አለሚቱ፡** ጎሣ ተው የበላይና የበታች ብሎ ነገር የለም፤ ወንድ የበላይ ሴት የበታች የሚል የለም፤ ምናልባት ባህላችን ዝም ብሎት ይሆናል፤ ቢሆንም ስህተቱ እየታረመ ነው። አሁንም ልጣላህ ፈልጌ ሳይሆን እስቲ

ጉልት ውዬ ስመጣ ሥራው ቁጭ ብሎ ይቆየኛል፤ ልጁም አብሮኝ ስለሚውል ተጎዳ፤ ልብሱም ይቆሽሻል፤ ትኩስ ምግብም አይመገብም። በዚህ ሰዓት እንደምታየኝ የስድስት ወር ነፍሰ ጡር ነኝ፤ ይህ ሁሉ ሲደራረብ በጣም ለኔ ጫና ነው፤ ላንተ ያላማከርኩ ለማን ለማክር።

1. ባልና ሚስቱ ወደድርድር የሚመጡ ይመስላችኋል?

**አቶ ጎሣ፡** ምን እያልሽ ነው?

**ወይዘሮ አለማቱ፡** እስቲ እኔን ሆነህ እየው።

**አቶ ጎሣ፡** አለሚቱ እሱማ እንድትጎጅብኝ አልፈልግም።

**ወይዘሮ አለሚቱ፡** ጎሳ ተጎዳሁ እኮ! እኔ የምልህ እንወያይ፤ እንስማማ፤ እንረዳዳ፤ እንተሳሰብ፤ ለሌላውም ምሳሌ እንሁን።

2. ባልዬው ሚስቱ እንደምታስበው ሀሳቡን የሚቀየር ይመስላችኋል?

**አቶ ጎሣ፡** አለም ምን ላድርግ?

**ወይዘሮ አለሚቱ፡** ጎበዝ አሁን ተስማማን፤ የምታደርገው የኔ ድካም ከተሰማህ ጥሩ ነው፤ ሌላውን ቀስ በቀስ እየተለማመድህ እንድትሄድ እንረዳዳለን።

**አቶ ጎሣ፡** አለም እስማማለሁ፤ እንመካከር።

**ወይዘሮ አለሚቱ፡** ይህ ለኔ ትልቅ ጉዳይ ነው፤ ስለዚህ ሥራ በሌለህ ጊዜ የልጁን ንጽህና ትጠብቃለህ፤ ልጁን ይዘህ እቤት ትውላለህ፤ እኔንም የሠራሁትን ታደንቅልኛለህ፤ ዋጋም ትሰጠዋለህ፤ እኔም የአንተን ሥራ አደንቃለሁ፤ ያገኘነውንም ገቢ በጋራ በጀት በማውጣት እንጠቀማለን፤ በዚህ ሁኔታ ከቀጠልን ከተረዳዳን ኑሯችንም ይሻሻላል፤ ፍቅራችንም የበለጠ ይጠነክራል።

**አቶ ጎሳ፡** አመሰግናለሁ! ሁሉንም ነገር በጋራ እንሰራለን "ከአንድ ብርቱ ሁለት መድሀኒቱ" የተባለው ለዚህ አይደለም? በዚህ ሁኔታ ልጃችንንም የሚወለደውንም በእንክብካቤ እንይዛለን። እኛም በደስታ እንኖራን ባል እና ሚስት አንድ አካል ማለት እንደሆነ አስረድተሸኛል በጣም አመሰግናለሁ።

**ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ**

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት "እውነት" ወይም "ሐሰት" በማለት መልሱ።**

1. በመጨረሻ ጎሳ ከሚስቱ ጋር ተስማምቷል።

2. የእነአለሚቱ ቤት የተሟላ እና የተስተካከለ ነው።
3. ጥሩ ትዳር እንዲሆን ባል እና ሚስት በመመካከር መኖር አለባቸው።

**ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ስሩ።**

1. የባልና ሚስቱ ድርድር በምን ምክንያት ተጀመረ?
2. በድርድሩ ውስጥ የተሻለ ሀሳብ ይቀርብ የነበረው በማን ነው?
3. የተሻሉ ሀሳቦች የምትሏቸውን ዘርዝሩ፣ መጥፎ ሀሳብ የምትሉትንም ጥቀሱ፡፡
4. የባልና የሚስቱ ድርድር በምን ተጠናቀቀ?

**ሐ. ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ከሰጣችሁ በኋላ ዓረፍተነገር መስርቱባቸው።**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ወሳኝ | ባልትና | አዛኝ | በጀት | ፈቃድ |

**ክፍለጊዜ፡ አስር**

## ተግባር ሁለት

**ከላይ በምንባቡ የቀረቡትን ገጸባህርያት (ባልና ሚስት) ምልልስ በጥንድ ጥንድ ሆናችሁ በማጥናት የባልና ሚስቱን ሚና ተከታችሁ ተውኑ።**

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ**

## ተግባር ሦስት

በባልና ሚስቱ ድርድር ጊዜ አቶ ጎሳ “ከአንድ ብርቱ ሁለት መድሀኒቱ” በማለት የተጠቀሙትን ምሳሌያዊ አነጋገር ፍች በቡድናችሁ ከተወያያችሁበት በኋላ ማብራርያውን በተወካያችሁ አማካኝነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት**

# ትምህርት አራት፡ መጻፍ

## ተግባር አራት

ሀ. እህትና ወንድም የጥናት ፕሮግራማቸውን ለመንደፍ የሚያደርጉትን ድርድር በመፍጠር የገጸ ባህሪያቱን ሀሳብ በመጻፍ ለመምህራችሁ አሳዩ።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሦስት**

ለ. የትምህርት ቤታችሁን የስነምግባር ደንቦች ከትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር በመጠየቅ በአንቀጾች ካደራጃችሁ በኋላ ለክፍል ተማሪዎች አንብቡ።

ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት

# ትምህርት አምስት፡ ቃላት

## መልመጃ ሶስት

ሀ. የሚከተሉትን ቃላት ከተመሰረቱበት የቃላት መጠን አኳያ በሰንጠረዡ ውስጥ መድቧቸው።

| ትምህርት ቤት፣ የከተማ ነዋሪዎች ማህበር፣ ዶክተር፣ ወይዘሮ፣ የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማህበር፣ ወታደር፣ የአፍሪካ ህብረት፣ መምህር፣ የዓለም የጤናድርጅት፣ ዓመተምህረት፣ ልብወለድ፣ የዓለም ዓቀፍ የትምህርት የባህልና የሳይንስ ድርጅት፣ የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብት ድርጅት የኦሮሚያ አደጋና መከላከል ዝግጁነት ኮሚሽን | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ከአንድ ቃል የተመሰረቱ | ከሁለት ቃላት በጥመራ ተመሰረቱ | ከሶስት ቃላት በጥመራ ተመሰረቱ | ከአራት ቃላት በጥመራ ተመሰረቱ | ከአምስት ቃላት በጥመራ የተመሰረቱ | ከስድስት ቃላት በጥመራ ተመሰረቱ |
| ወይዘሮ | ልብወለድ | የዓለም ጤና ድርጅት | | | |
| | | | | | |

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት

**ለ. ከላይ የተወያያችሁባቸውን ቃላትና ሀረጋት በምህጻር (አሳጥራችሁ) ጻፉ።**

**ምሳሌ፡ ትምህርት ቤት - ት/ቤት**

1. የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ
2. የከተማ ነዋሪዎች ማህበር
3. ዶክተር
4. ወይዘሮ
5. የኢትዮጵያ ቀይመስቀል ማህበር
6. የአፍሪካ ህብረት

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት

**ሐ. ከዚህ በታች በምህጻር የተጻፉትን በማራዘም ጻፉ።**

1. ዶር. 2. ወሮ. 3. ዓ/ም 4. ት/ቤት 5. ጽ/ቤት

**መ. የሚከተሉትን የረዘሙ ጽሑፎችን አሳጥራችሁ ጻፉ።**

**ምሳሌ፡ የኢትዩጵያ መድን ድርጅት - ኢ.መ.ድ**

1. የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበር
2. ጉልማሶች ማሰልጠኛ ጣቢያ
3. የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር
4. የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት
5. የኦሮሚያ ልማት ማህበር

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት**

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

## መልመጃ አራት

**ሀ. ከሚከተሉት ቃላት ቅጥያዎች በመነጠል አሳዩ**

ምሳሌ በላሁ - በላ-ሁ

1. ተሠራ
2. አስሮጠ
3. ቆላቸው
4. ተቀሰመ
5. ሄዳችሁ
6. ሰጠን
7. ተከፈተ
8. ተለወጠ
9. ቆረጠው
10. ቆፈረው

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

**ለ. በምሳሌው መሰረት ሰንጠረዡን አሟሉ።**

| ተ.ቁ | ቅጥያ ያለበት ቃል | ግንድ ወይም ዓምድ | ቅጥያ |
|---|---|---|---|
| 1. | አለፋቸው | አለፍ- | -አቸው |
| 2. | አስመታው | | |
| 3. | አልሄዱም | | |
| 4. | ተፈለጠ | | |
| 5. | አዘዘው | | |
| 6. | ሠራተኛ | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 7. | አስፈለጠው | | |
| 8. | ጠጣው | | |
| 9. | አስደነገጠ | | |
| 10. | ተፈለገ | | |

# ምዕራፍ ዘጠኝ፡ የመገናኛ ብዙኀን

**ክፍለጊዜ፡ አንድ**

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

**በዚህ ትምህርት ክፍል የማዳመጥ ክሂል መልመጃዎች እና ተግባራት ስለቀረቡ በትእዛዛቱ መሰረት በትኩረት ስሩ።**

### የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

1. የተለያዩ መረጃዎችን ለማግኘት የምንጠቀምባቸው ምን ምን ናቸው?
2. የመገናኛ ብዙኀን ጠቀሜታ ምን ይመስላችኋል?

### የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

**እያዳመጣችሁ የሚከተሉትን ስሩ**

1. ከመገናኛ ብዙኀን ጠቀሜታ __________እና______ ሊጠቀሱ ይችላሉ።
2. የመገናኛ ብዙኀን ጠቀሜታ እንዳላቸው ሁሉ ______አላቸው።
3. የተሳሳተ መረጃ በሰዎች መካከል______ይፈጥራል፡፡

## ክፍለጊዜ ሁለት

# የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

## መልመጃ አንድ

**ሀ. የሚከተሉትን ሀሳቦች "እውነት" ወይም "ሐሰት" በማለት በቃል መልሱ።**

1. ማህበራዊ መገናኛ በርቀት ያሉ ሰዎችን እንዲተዋወቁና እንዲግባቡ አጋጣሚ ይፈጥራል።
2. ማህበራዊ መገናኛ ሰዎች ትምህርታቸውን በርቀት እንዲከታተሉ ያደርጋል።
3. ማህበራዊ መገናኛዎች ሰዎችን በማዝናናት ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ።
4. የተሳሳተ መረጃ ማሰራጨት በሰዎች መካከል የሚፈጥረው ችግር የለም።
5. ማህበራዊ መገናኛ ሀገራት እንዲቀራረቡና የባህል ልውውጥ በመካከላቸው እንዲኖር ያደርጋል።

## ክፍለ ጊዜ፡ ሶስት

**ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ጽሑፍ መሰረት በቃል መልሱ**

1. የመገናኛ ብዙኀን ምን ምን ጠቀሜታ አላቸው?
2. የመገናኛ ብዙኀን የሚያደርሱት ጉዳት ምንድን ነው?

3. የመገናኛ ብዙኀን ትምህርትን ለማዳረስ አስተዋፅኦ የሚያበረክቱት እንዴት ነው?
4. የመገናኛ ብዙኀን የገበያ ትስስርን እንዴት ይፈጥራሉ?
5. የመገናኛ ብዙኀን አጠቃቀማችን ምን ሊሆን ይገባል ትላላችሁ?

**ክፍለጊዜ፡ አራት**

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### ተግባር አንድ

**የመገናኛ ብዙኀን ያለውን ጠቀሜታና ጉዳት በቡድናችሁ ከተወያያችሁ በኋላ በተወካያችሁ አማካኝነት ለክፍል ተማሪዎች በንግግር አቅርቡ።**

**ክፍለጊዜ፡ አምስት**


### ተግባር ሁለት

**የመገናኛ ብዙሃንን ጥቅምና ጉዳት በተመለከተ መምህራችሁ የሚያቀርቡላችሁን ግብዓት ካዳመጣችሁ በኋላ ሀሳቡን በየተራ እየተነሳችሁ ተናገሩ።**

ክፍለጊዜ ስድስት

# ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

## የመገናኛ ብዙኀን



### የቅድመማንበብ ጥያቄዎች

1. ከላይ ከተመለከታችሁት ስእል ምን ተረዳችሁ?
2. የመገናኛ ብዙሃን ምንድን ነው? ጠቀሜታውስ?
3. የምታውቋቸውን የመገናኛ ብዙኀን አይነቶች ስም ዘርዝሩ።

## የመገናኛ ብዙኀን ዓይነቶች

የመገናኛ ብዙኀን ዓይነቶች በርካታ ናቸው። ከነዚህ መካከል ሬዲዮን፣ ቴሌቪዥንን፣ ጋዜጣ፣ መፅሄትንና በራሪ ወረቀቶችን ለአብነት መጥቀስ ይቻላል። ሬዲዮ አለታዊ ዜናዎች፣ አዋጆች፣

ማስታወቂያዎች፣ መግለጫዎች፣ የተለያዩ ትምህርቶች፣ አዝናኝ ድራማዎች፣ ሙዚቃዎች ወዘተ ይተላለፉበታል። ማንኛውም በሬዲዮ የሚተላለፉ መረጃዎች በጆሮ የሚደመጡ ስለሆኑ ለተማሩም ሆነ ላልተማሩ ሰዎች እኩል ይሰራጫሉ።

ቴሌቪዥንም እንዲሁ በሬዲዮ የሚተላላፉት መረጃዎች ሁሉ የሚተላለፉበት ሲሆን ከሬዲዮ የሚለየው መረጃዎችን ከድምፅ በተጨማሪ በምስል የሚያቀርብ በመሆኑ ነው። በዚህም የተነሳ በበርካታ ሰዎች ተመራጭ ሊሆን ይችላል።

ጋዜጣ፣ መፅሄትና በራሪ ወረቀቶች ደግሞ ሁሉንም መረጃዎች በህትመት የሚያስተላልፉ የመገናኛ ዘዴዎች ናቸው። በነዚህ የመገናኛ ዘዴዎች አማካይነት ተገቢ መረጃዎችን ለማግኘት መረጃዎቹ በሚታተሙባቸው ቋንቋዎች የማንበብ ችሎታ እንዲኖር ያስፈልጋል።

ጋዜጣ በአብዛኛው በእለት ወይም በሳምንት መረጃዎችን ለአንባቢዎች ያደርሳል። በጋዜጣ ከሚተላለፉት መረጃዎች መካከል ዜና እና የተለያዩ ማስታወቂያዎች ዋነኞቹ ናቸው። መፅሄት ግን እንደጋዜጣ ሁሉ መረጃዎችን በቀን ወይም በሳምንት አያስተላልፍም። በመፅሄት የሚተላለፉት መረጃዎች እንደየሁኔታው በወራት ልዩነት ወይም በአመት አንድ ጊዜ ብቻ

ሊሆን ይችላል። በዚህም የተነሳ የመረጃዎቹ ዓይነቶች በጋዜጣ ከሚተላለፉት የተለዩ ሊሆኑ ይችላሉ። የበራሪ ወረቀቶች ግን አጫጭር ትምህርቶች፣ አድራሻዎች፣ የተቋማት ዋና ዋና አገልግሎቶች ወዘተ የሚተላለፉባቸው በመሆናቸው እንደመፅሄትና እንደጋዜጣ በጊዜ የተገደቡ አይደሉም።

## የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች

**ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች እያነበባችሁ ባዶ ቦታዎችን ሙሉ።**

1. ከመገናና ብዙኀን አይነቶች _____፣______፣______፣ ሊጠቀሱ ይችላሉ።
2. የህትመት መገናኛ ብዙኀን የሚባሉት_____፣ ____ ፣ ____ናቸው።

ከላይ ከተጠቀሱት የመገናኛ ብዙኀን ዓይነቶች የተለየው ደግሞ ኢንተርኔት ነው። ኢንተርኔት በፅሁፍ፣ በምስልና በድምፅ አማካይነት መረጃዎች እጅግ ፈጣን በሆነ መንገድ ያስተላልፋል ። የኢንተርኔት መረጃዎች በጊዜና በቦታ የተገደቡ አይደሉም። የተለያዩ ኮምፒዉተሮችንና ሞባይሎችን በመጠቀም በመረጃ መረቦች አማካይነት መረጃዎችን ከየትኛውም የዓለም አገሮች በአጭር ጊዜ ማንኛውንም መረጃ ማግኘት ይቻላል። በዚህም

የተነሳ ከሌሎቹ የመገናኛ ብዙኀን ዓይነቶች መካከል በቀዳሚነት ተመራጭ እየሆነ መጥቷል።

በአጠቃላይ መገናኛ ብዙኀን በሰው ልጆች መካከል የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር በማድረግ፣ ሰዎችን በማስተማርና በማዝናናት ወዘተ በርካታ ጠቀሜታዎች አሏቸው። በተለይም በአሁኑ ጊዜ የመረጃዎች አስፈላጊነትና ጠቃሚነት እየጨመረ በመምጣቱ የመገናኛ ብዙኀን ተፈላጊነትም በዚያው መጠን ጨምሯል። በአሁኑ ጊዜ በመገናኛ ብዙኀን አማካይነት የዓለም ህዝቦች ይበልጥ እየተግባቡና እየተዋወቁ፣ ባህላቸውንና እውቀታቸውን እየተካፈሉ ይገኛሉ።

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

**ሀ. የሚከተሉትን ሀሳቦች "እውነት" ወይም "ሐሰት" በማለት በቃል መልሱ ።**

1. በራሪ ወረቀቶች ከመገናኛ ብዙኀን አይመደቡም።
2. ቴሌቪዥን መረጃን በድምፅና በምስል ማስተላለፍ ይችላል።
3. ጋዜጣ ከህትመት መገናኛ ብዙኀን ይመደባል።
4. ኢንተርኔት ለመጠቀም ከሚያስፈልጉ ነገሮች አንዱ

ሞባይል ነው።

5. ከሁሉም የመገናኛ ብዙኀን ፈጣኑ በራሪ ወረቀት ነው።

**ክፍለጊዜ፡ ስምንት**

**ለ. በምንባቡ መሰረት ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ።**

1. ከሚከተሉት ውስጥ ከህትመት መገናኛ ብዙኀን የማይመደበው የቱ ነው?

   ሀ. ስልክ　　　ሐ. መጽሔት

   ለ. በራሪ ወረቀት　　　መ. ጋዜጣ

2. መረጃዎች በፅሁፍ፣ በምስልና በድምፅ አማካይነት እጅግ ፈጣን በሆነ መንገድ የሚያስተላልፈው የቱ ነው?

   ሀ. መጽሔት　　　ሐ. በራሪ ወረቀት

   ለ. ኢንተርኔት　　　መ. ሬድዮ

3. ቴሌቪዥን ከሬድዮ የሚለየው በምንድነው?

   ሀ. የህትመት የመገናኛ ብዙሃን በመሆኑ

   ለ. በድምጽና በምስል መተላለፉ

   ሐ. በወር መቅረቡ

   መ. በጊዜ ባለመገደቡ

4. የበራሪ ወረቀት አገልግሎት

   ሀ. አጫጭር ትምህርቶችን ለማስተላለፍ

ለ. አድራሻዎችን ለመጠቆም

ሐ. የተቋማትን አገልግሎቶች ለመግለጽ

መ. ሁሉም መልስ ነው

5. በጊዜ የማይገደብ የመገናኛ ብዙሃን የቱ ነው?

ሀ. ቴሌቪዥን　　　　ሐ. ኢንተርኔት

ለ. ሬድዮ　　　　መ. መጽሔት

ሐ. ቀጥለው ለቀረቡት ቃላትና ሀረጋት አውዳዊ ፍች ስጡ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| በጊዜ የተገደበ | በራሪ | ቀዳሚ |
| አማካኝነት | በርካታ | |

ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

### ተግባር ሶስት

ሀ. ከላይ ካነበባችሁት ምንባብ ከየአንቀጾቹ ዋና ዋና ሀሳቦችን አውጥታችሁ በመፃፍ ለመምህራችሁ አሳዩ።

ክፍለጊዜ፡ አስር

ለ. የሚከተሉትን የመገናኛ ብዙኀን አገልግሎትና ባህርይ በአጫጭር ዓረፍተነገር ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡ ሬዲዮ፡ ሬዲዮ በጆሮ የሚደመጡ መረጃዎችን

በአየር ሞገድ ያስተላልፋል፡፡

| ቴሌቪዥን፣ | ጋዜጣ፣ | መፅሄት፣ | በራሪወረቀቶች |
|---|---|---|---|

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ**

## ተግባር አራት

የኢንተርኔት አገልግሎት ምን እንደሆነና የሚሰጠውን ጠቀሜታና የሚያስከትለውን ጉዳት ሌሎች ሰዎችን በመጠየቅ ያገኛችሁትን ሀሳብ ፃፉና ለክፍል ተማሪዎች አንብቡ።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት**

## ተግባር አምስት

ወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች ወይም ወቅታዊ የስፖርት ክንውኖች በተመለከተ አጭር ዜና ፃፉ። የፃፋችሁትን መምህራችሁ በሚሰጧችሁ እድል ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሶስት**

# ትምህርት አምስት፡ ቃላት

## መልመጃ ሶስት

ሀ. የሚከተሉትን ቃላት ባነበባችሁት ምንባብ መሰረት አውዳዊ ፍች ስጡ።

ገደብ፣ ግለሰባዊ፣ አገልገሎት፣ ኅትመት፣
መረጃ፣ ፈጣን፣ ሙ.ያ፣ ቀዳሚ፣ ማሠራጨት

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት

**ለ የሚከተሉትን ቃላት በክፍት ቦታ ውስጥ በማስገባት አረፍተነገሩን አሟሉ።**

ታዳሚዎች፣ ኮምፒውተር፣ ምስል፣ ትኩረት፣ መረጃ

1. የስብሰባችን_______ጠቃሚ አስተያየቶችን ሰጡ።
2. ታሪክ ለመጻፍ ተጨባጭ _______ሊኖር ይገባል።
3. ዘመናዊና በፍጥነት ለመፃፍ የሚያገለግል መሳሪያ______ ነው።
4. የአድማጭን _______ የሚስብ ንግግር አደረገች።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋሰው

## መልመጃ አራት

**ሀ. ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ቅጥያዎችን ለይታችሁ አውጡ።**

ምሰሌ፡ የኮሮና ቫይረስ ስርጭት ስለተባባሰ የፊትና የአፍንጫ መሸፈኛ መጠቀም አላቋረጥንም። **ቅጥያ -- ስለ**

1. መገርሳ አባቱ ስለመጣ አብሮት ሄደ።

2. አያንቱ በአውሮፕላን ተሳፍራ መጣች።
3. ወፎች ዛፍ ላይ ይኖራሉ።
4. ዝናብ ስለመጣ በረንዳ ስር ተጠለልኩ።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት**

**ለ. የሚከተሉትን ቅጥያዎችን በመጠቀም አረፍተነገር መስርቱ።**

**ምሰሌ፡ ወደ -   በሻዱ ወደገበያ ሄደች ።**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ላይ፣ | ሥር፣ | ጋር፣ | ውስጥ |

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት**

**ሐ. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በቅጥያዎች አሟልታችሁ ጻፉ**

1. ቤታችን _______ ትምህርት ቤታችን ይርቃል።
2. መጽሐፉን ጠረጴዛ _______ አስቀምጥ!
3. ከበደ ውሻውን _______ ዱላ መታው።
4. ነቀምቴ ውብ ከተማ _______ ሆነች ትማርከኛለች።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

**መ. ከሚከተሉት ዓረፈተነገሮች ውስጥ ቅጥያዎችን በመለየት አውጡ።**

1. ከጅማ ወልቂጤ ድረስ አስፓልት መንገድ ነው።

2. ቢሾፍቱ በሞጆና በአዳማ መካከል ይገኛል።
3. ስለ ትምህርት ማሰብ ጥሩ ነው ።
4. ሁሉም ሰው የሀገር ፍቅር ሊኖረው ይገባል።
5. እጅን በአልኮል ማፅዳት የኮሮና ስርጭትን ለመከላከል ይጠቅማል።

# ምዕራፍ አስር፡ ንግድ

## ክፍለጊዜ፡ አንድ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

**በዚህ ትምህርት ክፍል የማዳመጥ ጽሁፍ፣ የተለያዩ መልመጃዎች እና ተግባራት ስለቀረቡላችሁ በተሰጡት ትዕዛዛት መሰረት በትኩረት ስሩ።**




### የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. ከምስሉ ላይ የተረዳችሁትን ለመምህራችሁ ተናገሩ።
2. በቤታችሁ ወይም በመኖሪያችሁ አካባቢ ያሉ ነጋዴዎች ምን ምን ይነግዳሉ?

3. በንግድ ስራ ላይ ለመሰማራት የንግድ ፈቃድ ያስፈልጋል ብላችሁ ታስባላችሁ? ለምን?
4. ስታዳምጡ አዳዲስ ቃላትና ዋና ዋና ሀሳቦችን መዝግቡ።

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ወይዘሮ ጫልቱ እና አቶ ረጋሣ ሁለቱም በ________ሥራ ተሰማርተው ይሰራሉ።
2. በአንድ ወቅት ወይዘሮ ጫልቱ እና አቶ ረጋሣ______ባለመክፈላቸው ሱቃቸው ታሽጎ ነበር።
3. ሱቃቸው ለምን እንደታሸገ ለመረዳት በአካባቢው ወደሚገኝ________ሂዱ።
4. ግብር መክፈል ሀገሪቱ የጎደላትን _______ ለማሟላት እንደሚያስችል ጠንቅቀው አውቀዋል።

**ክፍለጊዜ፡ ሁለት**

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

**ሀ. ባዳመጣችሁት መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች “እውነት” ወይም “ሐሰት” በማለት በቃል መልሱ።**

1. አቶ ረጋሣ እና ወሮ ጫልቱ ወንድም እና እህት ናቸው።
2. ግብር መክፈል የዜግነት ውዴታም ግዴታም ነው።

3. ትክክለኛ ግብር ለመገበር የእለት ገቢንና ወጪን መመዝገብ አስፈላጊ ነው።
4. በግብር ከፋይነታቸው ሽልማት ያገኙት ወይዘሮ ጫልቱ ብቻ ናቸው።
5. በአቶ መገርሳ አካባቢ የሚመረተው ፍራፍሬ ነው።
6. እነወይዘሮ ጫልቱ ህጋዊ ነጋዴ ስለሆኑ ደስተኞች ናቸው።

**ክፍለጊዜ፡ ሶስት**

**ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ጽሑፍ መሰረት በቃል መልሱ።**

1. የአቶ መገርሳ ስራ ምንድን ነው?
2. ወይዘሮ ጫልቱ እና አቶ መገርሳ ስንት ልጆች አሏቸው?
3. ግብርን መክፈል ለምን ይጠቅማል?
4. አንድ ነጋዴ ህጋዊ የሚባለው ምን ሲያሟላ ነው?

**ክፍለጊዜ፡ አራት**

**ሐ. ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሰረት አውዳዊ ፍች ስጡ።**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ገቢዎች፣ | ማደስ፣ | ተሸላሚ፣ | ምርት፣ |
| ሸቀጣሸቀጥ፣ | ውዴታ፣ | ሱቅ | ግዴታ |

**ክፍለጊዜ፡ አምስት**

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር


### ተግባር አንድ

ሀ. ስታዳምጡ የመዘገባችኋቸው አዳዲስ ቃላትና ዋና ዋና ሀሳቦች ላይ በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ ለክፈሉ ተማሪዎች በቃል ተናገሩ።

ለ. በአካባቢያችሁ የሚከናወኑ ንግዶች ምን እንደሆኑ ሰዎችን በመጠየቅ ከአደራጃችሁ በኋላ ለክፍል ተማሪዎች በንግግር አቅርቡ።

**ክፍለጊዜ፡ ስድስት**

## ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ



## ቅድመማንበብ ጥያቄዎች

1. ከምስሉ የተረዳችሁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።
2. በአከባቢያችሁ ከሚገኙ ነጋዴዎች ምንምን ዕቃዎችን ገዝታችሁ ታውቃላችሁ?
3. ቀጥሎ የሚታነቡት ምንባብ ስለምን የሚያወሳ ይመስላችኋል?

## ንግድ

ንግድ ማለት የምርት ውጤቶች በመግዛት እና በመሸጥ ልውውጥ ውስጥ ትርፍ ለማግኘት የሚደረግ ሂደት ነው። ከዚህ የሚገኝ ትርፍም ከሀብት ማግኛ መንገዶች ውስጥ አንዱ ነው።

የንግድ ሥራ ዘርፍ ለማከናወን ራሳቸውን የቻሉ ሕጎች አሉት። ከነዚህ ሕጎች መካከል አንዱ የንግድ ፈቃድ ማውጣት ነው። አንድ የንግድ ፍቃድ የሚሰጠው ለአንድ የስራ ዘርፍ ብቻ ነው። የንግድ ፈቃድ የሚሰጠው ሰው ሕጋዊ በመሆኑ የህግ ከለላ ያገኛል። ምክንያቱም የንግድ ፈቃድ ይዞ የሚሰራ አካል ለሕግ ተገዥ በመሆኑ ነው።

1. ህጋዊ ነጋዴ የሚበላው እንዴት ያለ ነጋዴ ነው?
2. ግብር መክፈል ለምን ይጠቅማል?

ንግድ ፈቃድ ያለው ነጋዴ ሥራው እንዳይስተጓጎል ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት። ምክንያቱም አንድ ነጋዴ ህጋዊ ነው የሚባለው ግብሩን በአግባቡ ሲከፍል ብቻ ስለሆነ ነው። መንግስትም ከዚህ በሚገኘው ገቢ እንደመንገድ፣ መብራት፣ ውሃ የመሳሰሉትን መሰረተልማቶች ስለሚሰራበት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የትምህርት የጤና ወዘተ ተቋማትን ለማስፋፋት ይገለገልበታል። ግብር ከፋዮች ከአቅማቸው በላይ ወይም በታች እንዳይከፈሉ ነጋዴዎቹ ገቢያቸውን እና ወጪያቸውን በአግባቡ ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል፤ በዚህም መሰረት የንግድ ፈቃድ ማደሻ ጊዜ ሲደርስም ማሳደስ ግዴታቸው ነው።

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**

## መልመጃ ሁለት

**ሀ· የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት “እውነት” ወይም “ሐሰት” በማለት በቃል መልሱ።**

1. ንግድ ማለት ሰዎችን እያታለሉ መገብየት ነው።
2. ምርትን በመግዛት እና በመሸጥ ትርፍ ማግኘት ንግድ ይባላል።
3. ንግድ ለመነገድ የንግድ ፈቃድ ያስፈልጋል።
4. አንድ ነጋዴ የስራ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት።

**ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ።**

1. **አንድ ነጋዴ ፈቃድ ማውጣቱ የሚጠቅመው**

   ሀ. እንደፈለገው ዋጋ ጨምሮ ለመሸጥ ነው።

   ለ. የህግ ከለላ ለማግኘት ነው።

   ሐ. ህዝቡን ለማታለል ስለሚረዳው ነው።

   መ. ከቁጥጥር ውጭ ስለሚሆን ነው።

2. **ግብር መክፈል ጥቅሙ ምንድነው?**

   ሀ. መሰረተ ልማቶችን ለማስፋፋት

   ለ. ከዋጋ በላይ ለመሸጥ

   ሐ. ዕቃን ደብቆ ለማቆየት

   መ. ሁሉም መልስ ነው

3. **የንግድ ሥራ እንዳይስተጓጎል ከሚከተሉትን አንዱ አስፈላጊ ነው።**

   ሀ. ዕቃ በብዛት ማስገባት

   ለ. የንግድ ፈቃድ ማደስ

   ሐ. ብድር አለመክፈል

   መ. ደንበኛን አለማብዛት

4. **የአንድ ሀገር በጀት በአብዛኛው የሚገኘው ከየት ነው?**

   ሀ. ከእርዳታ　　　ሐ. ከግብር

   ለ. ከመዋጮ　　　መ. ከመንግስት

5. **ግብር ከፋዮች የሚከፍሉት ግብር ከአቅማቸው በላይ ወይም**
   በታች እንዳይሆን ምን ማድረግ አለባቸው?
   ሀ. ከገቢዎች ጋር መግባባት
   ለ. ገቢያቸውን መደበቅ
   ሐ. ደንበኞቻቸውን መቀነስ
   መ. ገቢ እና ወጪያቸውን ማሳወቅ

**ክፍለጊዜ፡ ስምንት**

**ሐ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በቃላችሁ መልሱ**

1. አንድ ነጋዴ ፈቃድ ባይኖረው ምን ይገጥመዋል?
2. ግብር መክፈል ጥቅሙ ምንድነው?
3. የንግድ ፈቃድ ማሳደስ ለምን ያስፈልጋል?
4. ሕገ ወጥ ነጋዴ እንዴት ያለ ነው?
5. አንዲት አገር እንድታድግ ከሚረዳው አንዱ ምንድነው?

**ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ**

# ትምህርት አራት፡ መጻፍ

## መልመጃ ሶስት

**የሚከተሉት ቃላት ከምንባቡ ውስጥ የሚገኙባቸውን ዓረፍተነገሮች በመለየት ጻፉ።**

1. ንግድ
2. አገልግሎት

3. ላቅ
4. ተቋም
5. ልውውጥ
6. ሕግ
7. ተገኘ
8. ትርፍ
9. ሀብት

**ክፍለጊዜ፡ አስር**

## ተግባር ሁለት

**ከዚህ በታች የቀረቡት ሃሳቦች ቢደራጁ አንድ የተሟላ አንቀጽ ይመሰርታሉ፤ በመሆኑም ሀሳቦቹን አደራጅታችሁ ጻፉ።**

1. ደብተሩን የገዛሁበት ዋጋ ከሁሉም ከፍተኛውን መጠን ይይዛል።
2. ሱቅ ሄጄ የተለያዩ የትምህርት መሳሪያዎች ገዛሁ።
3. በአጠቃላይ እነዚህን አስፈላጊ የሆኑትን የትምህርት መሳሪያዎች ለመግዛት ሱቅ ሄጄ ያወጣሁት ብር 50 ብር ነው።
4. የላጲስ ዋጋ ከሁሉም አነስተኛውን ብር ወስዷል፤ ዋጋውም 5 ብር ነው።
5. የገዛኋቸውም ደብተር፣ ማስመሪያ እና ላጲስ ናቸው።
6. ደብተሩ የተገዛበትም 30 ብር ነው።

7. ከደብተር ቀጥሎ ከፍተኛውን ዋጋ የወሰደብኝ ማስመሪያ ሲሆን የተገዛበት ዋጋም 15 ብር።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ**

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

### መልመጃ አራት

**ሀ. ለሚከተሉትን ቃላት ሁለት ፍቾ ስጡ።**

ምሳሌ፡ ደረሰ - ቀረበ / ደረሰ - ጻፈ

ተኩላ፣ ጠራ፣ ቆላ፣ አጠረ፣ ሰፈረ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት**

**ለ. ከላይ ሁለት ሁለት ፍቾ በሰጣችኋቸው ቃላት አስር አረፍተነገሮች መስርቱ**

**ምሳሌ፡ የእሬቻ በዓል ደረሰ።**
ዳባ ወዬሳ ጎዳኒሳ የተባለውን ልቦለድ መጽሃፍ ደረሰ።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሶስት**

**ሐ. በሚከተሉት ቃላት ባዶ ቦታዎች በማሟላት ጻፉ።**

ቀለበ/ቀለበች፣ ቋጨ/ቋጨች፣ ጠመደ/ጠመደች፣ ቀጨ/ቀጨች

ምሳሌ፡ ገመዳ ኳሱን <u>ቀለበ</u>።
ተሊሌ በሬው እንዲወፍር <u>ቀለበች</u>።

1. ተሰማ በሬዎቹን ለእርሻ------።

2. ጓደኛዬ ወንድሙን በነገር -------።
3. አለሚቱ አክርማ -------።
4. ወንጀለኛው የሰላማዊ ወጣቶችን ህይወት በአጭር------።
5. እርግቤ ነጠላውን --------።
6. መምህራችን ንግግሯን በአጭሩ ------።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት**

**መ. ሁለት ፍች የሚሰጡ ቃላትን ለዩ።**

| | | |
|---|---|---|
| መገበ | ገደበ | ጋገረ |
| ደወለ | ዳበሰ | ደቀቀ |
| ደገነ | ገደለ | ዋለለ |
| ከበበ | ገመደ | ነቃ |

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት**

**ሠ. በክፍለጊዜ አስራ አራት ‹መ› ስር የለያችኋቸውን ሁለት ሁለት ፍች ያላቸውን ቃላት ፍቻቸውን ጽፉችሁ ለክፍል ተማሪዎች አንብቡ፡፡**

**ምሳሌ፡ ገደበ፡** በላይ የክረምት ውሀ **ገደበ፡፡**

የስብሰባው መሪ የተሳታፊውን ሀሳብ **ገደበ፡፡**

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት**

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

## መልመጃ አምስት

ሀ. በሰንጠረዥ ያሉትን ቃላት ቅጥያዎች ለዩ።

| ተ.ቁ | ቃል | መነሻ ቅጥያ | ነጻ ቃል | መድረሻ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | በሬውን | በ | በሬ | ውን |
| 2. | ሀቀኛ | | ሐቅ | ኧኛ |
| 3. | ታዳሚዎች | | | |
| 4. | አሰፈጠረ | | | |
| 5. | ቤተሰባዊ | | | |
| 6. | እንደራስህ | | | |
| 7. | አልመጣም | | | |
| 8. | በፍጥነት | | | |

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት**

ለ. ቅጥያ ያላቸውን ቃላት ለዩ።

ምሳሌ፡ ሰማያዊ (ሰማይ - አዊ)

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሰካራም | ሀገራዊ | ሕዝብ | ሰማያዊ |
| ላም | በሬው | ሠራተኛ | |
| አይናማ | ቤት | ሰማይ | |
| ልብ | ነገረኝ | መምህራን | |

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

ሐ. ከላይ በ‹ለ› ስር በለያችኋቸው ቃላት ዓረፍተነገር መስርቱ።

ምሳሌ፡ ሰማያዊ - ሰማያዊ ቀለም ያለው ልብስ ምርጫዬ ነው።